1. የፕሮቴስታንት “ኃይማትኖት” ቆርቋሪ ማርቲን ሉተር ማን ነው?

ዛሬ መንፈሳዊ ኪሳራ ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያ ን እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ እንደ ሳንባ ቲቢ፣ እንደ ወባ፣እንደ ግደለሽነት፣ እንደ ሞራል መበስበስ እንደ ጥገኝነት እንደ ፍርሃት እንደ ቀቢፀ ተስፋ እንደ በራስ አለመተማመን እንደ መጸየፍ እንደ መላቢስነት እንደ ረሃብ ችኩ አጥለቅልቆታል። በኤርትራ ከራስ (ከኢትዮጵያዊነት) መቦደስ የተጀመረው በኢትዮጵያዊነት የማፈርና ኢትዮጵያዊ ውርስን የመክዳት ሂደት ያስከተለው መንፈሳዊ ኪሳራ በተቀረው የሀገራችን አካባቢዎች እውን ይሆን ዘንድ ሕዝባችን በሥነ-ልቡና ለማዘጋጀት በአሁን ጊዜ አነጋገር የደቡብ ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልልና በኦሮሚያ ውስጥ በተለይም ምዕራባዊና መካከለኛው የኦሮሚያ ግዛቶች በሚባሉት አካባቢዎች እዲሁም የመሃልና የሰሜኑን የሀገራችን ክፍልም በታሪካችን ውስጥ አይተነው በማናውቀውፍጥነት እያጥለቀለቀ ነው።

ከፍተኛ የዶላር ሠራዊት ታግዘው በዘመናዊ ሳይኮሎጂ (modern psychology) የባሕርይ ሳይንስ (behavioral science) የጭንቅላት ሳይንስ (neuro science) ከዚያም በከፋ መልኩ በምዕራብ አውሮፓና በሰሜን አሜሪካ የማይፈለገውን የአሳቦት መግቻ /የጭንቅላት ማንጠፊያ/ የባሕርይ መገደቢያ ዘዴዎች (thought/mind control techiniques) በመጠቀም ሥነ-ልቡናዊ ከለሳዊ የመቦዳደስ ሂደቱን በአዲስ ኃይል በተቀረው የሀገራችን ክፍሎች ለመድገም በሎተራዊ ወኔ ደፋ ቀና የሚሉ ምዕራባውያን ሚሲዮኖችና የዕርዳታ ድርጅቶች ሀገራችን ውስጥ ሸርጉድ ማለት ከጀመሩ ቆዩ። ለዚሁ ክፋ ተግባርም የአጥንታችን ፍላጭ የሥጋችን ቁራጭ በኾኑ ወገኖቻችን በፕሮፓጋንዳና በአዕምሮ ማንጠፍ ሥራ በማሰልጠን በአለፉት 500 ዓመታት በቀጥታ ወታደራዊ ጅሀድ መፍጠር ያልቻሉ ሥነ-ልቡናዊ፣ ሥነ-ምግባራዊ፣ ሥነ-መለኮታዊ... ጥገኝነት በሕዝባችን ናላ ውስጥ ለመፍጠር እንዲሁም ድሮ የተከሉትን የጎሳ ንቃተ ኅሊና (consciousncss) በአዲስ መልክ ለመቀስቀስ የሀገራቱን ለውጭ ድርጅቶች ክፍት መሆን እንደ ወርቃማ እድል በመቁጠር በአሰፈሪና ጅሀዳዊ ወኔ እየተንቀሳቀሱ ይገኛል።

እነዚህም ታሪካዊ ጠላቶቻችን ምዕራባውያን የገሃነም ደጆች በፍቅርና በእውነት ስም ሕዝባችን እንዲጋተው የፈረዱበት የነጭ ዘር የበላይነት ማረጋገጫ ክፋ ዜና የሚሰበከውና የሚመራው በ 66 ከሌሎች መጻሕፍ ተለይተው “በእግዚአብሔር በተገለጹ” ቅዱሳን መጻሕፍት (እንደ እውነቱ ከኾነ በማርቲን ሉተር የተገለጹ) ስም ነው። ተፈጻሚ የሚኾነው ደግሞ በግል ፍርድ “በእምነት ብቻ” “በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ” “በሚያስተማምነው የገነት መግቢያ” ትኬትና መሰል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልኾኑ

እምነቶችን መገለጫቸው አድርገው በሚንቀሳቀሱ ስመ ቁጥረና እምነተ ብዙ ፕሮቴስታንታዊ "ሃይማኖቶች" ስም ባንገቡ ድርጅቶች አማካኝነት ነው።

ፕሮቴስታንታዊ ጽንፈኞች በከተማዎቻችን፣ በገጠሮቻችን በአፍሪካ የስደተኞች ካምፖች በዐረቡ የዓለም ክፍል በአውሮፓ እንዲሁም ሰሜን አሜሪካ ውስጥ በአጭሩ ወገኖቻችን በሚኖሩበት ቦታ ኹሉ የአቅመቢስነት ፕሮፓጋንዳዎች ይነዛሉ። በዚህም የተነሳ አንድ ዘር፣ አንድ ሕዝብ፣ የአንድ ኢትዮጵያ ዜጋ ለማመን በሚያስቸግር የልዩነት እምነቶች በመታቀፋ ዛሬ ሥነ-ልቡናዊ መራራቅ በሕዝባችን ውስጥ ከመፈጠሩም በላይ አንዳንድ ወገኖቻችን ራሳቸውን ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለዩ ዘሮች አድርገው እንዲያዩና ስለዚህም መገንጠል እንደሚገባቸው እያሳመኗቸው ይገኛሉ።

እንቆቅልሹ ታዲያ በስደት ቦታ የሚደርስበት ማንነታዊ መሳደድ የጥቃቱ መጠንና ጥልቀት የአጀማመሩና ያጨራረሱ ሥነ-ምግባራዊነት መጉደልና አዳኝ አውሪያዊነት ደረጃ ሀገራችን ውስጥ እየተፋፋመ የመጣው የፕሮቴስታንታዊ ጀሃድ ያህል አጥለቅላቂ አለመኾኑ ነው።

ስደት ስደት በመኾኑና በሰው ደግሞ የህገርን ያህል መብት አይገኝም ተብሎ ስለሚገመት "መንፈሳዊ ሽብሩ" የፕሮፓጋንዳ ገዥዎቹ ቁጥርና ቁርጠኝነት በዚያው ልክ ይበዛል ብሎ መጠርጠሩ አይደንቅም። ይሁንና በማናለብኝኛዊ በማንን ፈርቾ ተጋፊ አሠራሩ የሚረብሽ እጅግ ስሜታዊና ጅምላ ማንነታዊ እልቂት የሚፈጸም በንቀቱ ሉተራዊ እምነቱና ዶላራዊ ኪሱ የከበደ አብዮታዊ ተቃውሟዊ/ ፕሮቴስታንታዊ እንቅስቃሴ ከውጭ ሀገር/ስደት ላይ ይልቅ ኢትዮጵያውያንን ሀገራቸው ላይ የበለጠ ያዋርዳል። ይህ እጅግ እንቆቅልሽ ወዲያውም ግን መራራ እውነታ ነው።

"ሰው በሀገሩ ቢበላ ሽንበቆ መቆመቆ ይከበር የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ" የሚለው ሽለላ ከትናንት ጋር አብሮ ማለፉንና ዛሬ ደግሞ "ሰው በሃገር ሰው በወንዙ ቢያምን በአንዷ ሃይማኖት በጥንቷ ተዋሕዶ.. ይዋረድ የለም ወይ ጎልውናው ተክዶ" በሚለው መተካቱ በሀገሬና በማንነቴ በነገ ልጆቼና የልጅ ልጆቸ ላይ የሚደርሰው ከፍተኛ መፋለስ ያገባኛል የሚል ሕይወትን ነጻነትን ከክብርና መልካም የአንድነት እሣቤአብሔራዊ ውርስን ከአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታነት በላይ የአንድ ነገር ውሕደት መሆናቸውን የተረዳ ዜጋን ኹሉ የሚያስቆጭ፣ የሚያሳፍር፣ የሚያስፈራ ዕረፍት የሚነሳ ነው።

ይህ ማቆሚያ ጊዜና መሸሸጊያ ቦታ የሌለው የሚመስል አስከፊ ፕሮቴስታንታዊ አክራሪ ጥቃት በኃላፊነት የሚሰማውን ኹሉ እንዴት ከዚህ ጅምላ አልቂት እሣቤአብሔርን፣ ቤተሰብን፣ ሀገሬን፣ ሕዝቤን፣ ልታደግ? ብሎ በፍቅር እንዲነሳ ያደርጋል። የሚያዩትን ጨለማ ነገር አለመውደድና ግን ደግሞ ይህን ጨለማ አለመቃወም ከፍቅር ሊሆን አይችልም በፍፁም። ፍርሃትን ይዞ ፍቅር አለኝ ማለት አይቻልምና። የፍቅር ትርጉሙ ይኸው ነውና። የአባቶች ሃይማኖት የሚለው በፍቅር ፍርሃት የለም ነው። ሀገሬን፣ ቤተሰቤን የቀጣይነቱ ማረጋገጫ ውርሴን እወዳለሁ ማለትና ወዲያውም በጨለማ

ሲወረሩ የፍቅር ብርሃንን አለማብራት በፍፁም በፍጻም ከፍቅር ሊሆን አይችልም። ፍቅር እምነትና የማንነት ግንዛቤ ውስጣችን ባለመኖራቸውም ይመስለኛል።

በራሳችን ሀገር ውስጥ የሚደርስብንን የመሳደድና እንደገና የመወለድን ፕሮቴስታንታዊ ሞት ተጋቱ ስንባል ወይም ሌሎች ምስኪን ወገኖቻችን እንዲጋቱ/እንዲንበረከኩ በመናፍቃን ከፍተኛ ግፊት ሲደርስባቸው እያየን እንዳላየን ዝም የምንል።

ፕሮቴስታንታዊ ስም ያላቸውና (በተለይ አንዳንዶቹ ምንም ክርስቲያናዊ ሊባል የሚችል እምነት የሌላቸው) ግን የኢየሱስ ነን የሚሉ የተቃውሞ ሠራዊቶች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ቀድሞ የመውረርንና ቀድሞ የመግደልን ክብር ለማግኘት ውድድር ላይ ያሉት ከኤች አይ ቪ ኤድስ ጋር ይመስላል። ስኬታቸው አስፈሪ ነው። የጨለማ ሠራዊቶች በሽብራዊ ፕሮፖጋንዳቸው ዐረቦችን፣ ቱርኮችን፣ፖርቹጋሎቹን፣ ፋሽታዊት፣ካቶሊካዊት ጣሊያንንና ሞሶሌንን በሚያስገርምና በሚያስቀና ኹኔታ በጨለማ ፍጥነት እየተጓዙ ሕዝባችንን በማንበርከክ ላይ ይገኛሉ። እነዚህ የተቃውሞ አብዮት ፕሮቴስታንቲዝም ተከታዮች በክርስትና እምነት ስም በሕዝባችን ሕይወት ውስጥ ከሚነዙት ጨካኝና ዘረኛ የመለያየት ክፉ ዜና ከተደገሰልን የማንነት ሞት መዳን ይገባናል። ታዲያ አክራሪ ፕሮቴስታንታዊነት ምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ውስጥ እንደወደቀ ኹሉ ቅድስት ኢትዮጵያም ላይ ይወድቅ ዘንድ በመጀመሪያ የዚህን እምነት ቆርቋሪ ወይም መሥራች ማንነት ማወቅ ግድ ይላል። አልያ ጉዞአችን የጨለማ ጉዞ የሚኾነው።

የፈረንጆች ፀያፍ የኾነ አንድ ሕዝብን በንሳ በዘርና በሃይማኖት በማበላለጥ ከፋፍሎ የማጥመቅና ከፋፍሎ የመግዛት ሱሳቸው ይህን ያልተወለዳቸውንና የሚጠሉትን ሕዝብ በባርነት የመግዛት ጉምጀታ እውን ለማድረግ ሃይማኖትን ሳይቀር ከቅዱስነቱ ዝቅ በማድረግና በማርከስ ለዚህ እክይ ዓላማቸው እንደመሳሪያ ሲጠቀሙበት ማየት እጅግ ሊረብሸን ይገባል።

ከዚያ በላይ ገንዘብንና መሰል ከእግዚአብሔር ያልኾኑ ሃይማኖት ማስካጃ ዘዴዎችን በመጠቀም ሕዝባችን በራሱ ላይ እንዲያምጽ ራሱንና የራሱ የኾነውን ኹሉ እንዲጠላ ማድረግ መቻላቸው ከመረበሽ አልፎ ጎልውናችን አደጋ ላይ ጥሎታልና አንድ ነገር ማድረግ አለብን።

በኹሉም ታላላቅ ሃይማኖቶች የተከበረውና የግለሰቡም ኾነ የሀገር መሠረት የኾነው ቤተሰብ የእነዚእምነቶች የጥፋት ተልእ ዋና ኢላማ ነው። በክርስትና ቤተሰብ ትልቅና የተቀደሰ ቦታ አለው። አሜሪካውያን Families that pray together stay together. አብረው የሚጸልዩ ለቤተሰብ /ለጎብረተሰብ/ለሀገር ማጎናጸፍ ነው። ፈረንጆች ግን ለራሳቸው የሚፈልጉትንና በራሳቸው ቤተሰብ ላይ እንዲፈተጸም የማፈልጉትን ነገር በሌሎች ላይ መፈጸም ወደፊት ምዕራፍ ስድስት ላይ እንደምናየው የሚያምኑበት ውርሳቸው ነው።

ፕሮቴስታንታዊ ሥር መሠረት ያላቸው ጅሀደኞች የሚያደርጉት ቤተሰብን መብትን ነው። ይህም የእነዚህን ክፉ እምነቶች ሀገር የማጥፋት ተልእኮ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። የእነዚህን ገሃነማዊ የተቃውሞ የክርክር፣የጭቅጭቅ የመለያየትና የጦርነት ፕሮቴስታንታዊ “ሃይማኖቶች” ከምንጩ ከመሥራቹ ከማርቲን ሉተር ተልእኮ አንጻር ካልመረመርናቸውና መድኃኒቱንም ከበሽታው አንጻር ካልቀመምነው በቀር የሚፈጸምብንን የቤተሰብና የሀገር ማፈራረስ ኢ-ሰብአዊ ወንጀል እየታዘብን በእኩይነቱና በፀረ-ክርስቶስነቱ እየተገረምን አፋችንን ከፍተን ስናይ ስንሸበር ግራ ስንጋባ ስናለቅስ አቅመቢስነት ሲሰማን... እንኖራለን።

ኢየሱስና የኢየሱስን የምድር ሕይወት ትምህርት በመስቀል ላይ ሞቱን በሦስተኛው ቀንም ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ሳያውቁ ክርስቲያን መሆን ወይም ስለ ክርስትና ማወቅ አይቻልም። ስለ ማርክሲዝም ማወቅ የሚሻ የካርል ማርክስን ሕይወት ትግልና ትምህርት ለማወቅ ይገዳል። ያለ ማርክስ ማርክሊዝም አይሞከርምና። በዓለም ላይ የተፈጠሩ ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ፖለቲካዊ ወዘተ. እንቅስቃሴዎች ዅሉ ካለ ፈጣሪዎቻቸው /መሥራቾቻቸው ሕይወት የላቸው።

በኅብረተሰብ ታሪክ በየዘመኑ ብቅ የሚሉ መሪዎች በኅብረተሰብ ውስጥ የሚያመጡት ለውጥ እጅግ ጠቃሚና ገንቢ ወይም እጅግ አፍራሽ ውጤት ማስከተሉ በአያሌው የእነዚህን መሪዎች አስተዳደግ አኗኗር የአካልና የአዕምሮ ጤናና የሕይወት ልምድ ማወቅ ወሳኝ ነው። ከዚያም በላይ የዚህ ዅሉ ማሰሪያ የኾኑ ራሳቸውን ስለራሳቸው ማንነት ስለ ዓላማቸው እንዲሁም ለምሳሌ ስለ ሰው ልጅ፣ ስለ ዓለም፣ ስለ ታሪክ፣ ስለ ሕግ፣ ስለ ሰላም፣ ስለ ጦርነት፣ ስለ ቤተሰብ፣ ስለ ኅብረተሰብ፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ራስን መግዛት፣ ስለ መንፈሳዊነት፣ ስለ ፖለቲካዊ/ኢኮኖሚያዊ/ ማኅበራዊ ኹኔታዎች ወዘተ. ያላቸውን ግንዛቤ ከጻፉት ከተናገሩት ወይም ሌሎች የታሪክ ተመራማሪዎችና የቅርብ ደቀ መዝሙርቶቻቸው ስለ እነዚህ መሪዎች ከጻፉትና ከተናገሩት ማንነታቸውን መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው።

ውኃን ስለወረደ ብቻ አንጠጣውም መጀመሪያ ምንጩ ንጹሕ ወይም ቆሻሻ (መርዝ) መኾኑን ማወቅ አለብን። አልያ ሕይወትን ፈልገን የምንጠጣው ሊገድለን ይችላል። በጥላቻ፣ በቂምበቀል በስግብግብነት፣ በዘረኝነት፣ በጦርነት አምላኪነት በተሳሳተ ግንዛቤ በአምላክ የለሽነት በተሳከረ የአዕምሮ መንፈስ የተቀረቀሩ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች (social movements) ዅሉ በታሪክ ውስጥ ደጋግመን እንዳየነው ውጤታቸው አስከፊ ነው። ማርክሲዝም ሌኒንዝምን ፋሽዚዝምን ያስተውላል።

በ 1517 (አ.ኤ.አ.) የተጀመረው (ከአሁን በኋላ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተከተቡት ቀናት ዅሉ በአውሮፓውያን አቆጣጠር እንደኾኑ ይታወቃል። የኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲሆን እ.ኤ.አ. እጠቀማለሁ።) ከካቶሊዝም በአመጽ ተገንጥሎ የወጣውና አንድ ዓይነት ሕዝብ በመባል የሚታወቀውን ከፍተኛ የሀገሮች ጦርነትና አንድ ዓይነት ሕዝብ

በሚኖርበትም ሀገር ሳይቀር አስከፊና ትውልዶችን የዘለቀ እርስ በርስ እልቂት ያስከተለው ይኸው ጀርመናዊ አብት ፕሮቴስታንቲዝም ለምን እንደዚህ ዓይነት ዘግናኝ ውጤት እንዳመጣ ማንም ስለዚህ እንቅስቃሴ ማወቅ የሚፈልግ ዅሉ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው።

ዛሬ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚታየው የማያቋርጥ መበታተንና አልፎ አልፎም በአውሮፓና በተለይም አሜሪካ ውስጥ የሚስተዋለው በመንግሥትና የፕሮቴስታንት ሃይማኖቶች የተለያዩ ዲኖሚኔሽኖች (denominations) አክራሪ/ጽንፈኛ/ ክፍሎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶችና ደም ያቃቡ ውጤቶቻቸውን (ለምሳሌ በ 1980 916 ጥቁር አሜሪካውያንን ገድሎ የሞተው አሜሪካዊ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሪ ፈረንጅ ጂም ጆንስ በ 1993 ዌኮ ቴክሳስ አሜሪካ ውስጥ የፓስተር ደቪድ ኮረሽ ፕሮቴስታንት አማኞችና የአሜሪካ ምርመራ ቢሮ ተኩስ በመግጠማቸው 75 ሰዎች ሕጻናትን ጨምሮ ማለቃቸውን) ማሰብ ይበቃል። ዛሬ መጤ የባዕዳን አምነቶች ሀገራችንና ሕዝቦቿን ለተመሳሳይ መከራና እልቂት እያሰላለፏቸው ይገኛል።

በማርቲን ሉተር በ 1517 የጀመረው የመለያየት “ሃይማኖት” እና ያስከተላቸው ቀውሶችን በሚመለከት የምናነሳቸው ጥያቄዎች ዅሉ መልስ የሚያገኙት ከዚህ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ቆርቋሪ ሕይወትና መልእክት አንጻር ከተመረመሩ ብቻ ነው።

ማርቲን ሉተር ከልጅነት እስከ እውቀት በአእምሮ አለመረጋጋት ችግር ሲሰቃይ የኖረ ሰው ነው። ማርቲን ሉተር ማጣፊያው ሲያጥርበት “ሰይጣን” የሚለውን ቃል እንድ ማምለጫ ተጠቅሞበታል። ማርቲን ሉተር የሚቃወማቸውን ዅሉ ለመግለጽ ጸያፍና ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ቃላት በአንደበቱና በብዕሩ ያለ ገደብ በመጠቀሙም ይታወቃል። ማርቲን ሉተር አመክንዮ (reason) የሚጠላና የፍልስፍናውም ቁንጮ አድርጎ የተጠቀመ በጭፍን እምነት የተመራና ብዙ ሚሊዮን ተከታዮችንም ገደል ይዞ የገባ ሰው ነው። ማርቲን ሉተር ክርስቲያናዊ ባልኾነ ትምክህት የተወጠረ ዐመጸኛ ነው።

ማርቲን ሉተር ክርስቶስን የሚጠላና ተራ ሰው አድርጎ ለማቅረብም የጣረ ሐሳዊ - መሲህ ነው። ማርቲን ሉተር ኃጢአትን በተመለከተ እጅግ የተሳከረና ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኾነ እምነትን አኑሯል አስተማሯልም። ሉተር የክርስትናዊ ሕይወት መገለጫ የኾነው ራስን የመግዛት ችሎታ እንደ ሰማይ የራቀው ሰውም ነበር።

ይህ የታሪክ እንቆቅልሽ ግለሰብ የሴቶችን ሰውነት የካደና ለወንዶች ከሚሰጡት ወሲባዊ አገልግሎትና ልጆች ከመውለድ ውጭ ጥቅም እንደሌላቸው አድርጎ ተናግሯል። ትዳርንም ክርስቲያናዊ ክብሩንና ተልዕኮውን በመንፈግ ለወሲባዊ ርካታ ሲባል ብቻ በተቃራኒ ጾታዎች መካከል የሚኖር ዝሙታዊ የወሲባዊ ጥቅም ግንኙነት ብቻ አድርጎ በማቅረብ አዋርዶታል። ማርቲን ሉተር ከአንድ በላይ ማግባት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ሲል አስተምሯል። ማርቲን ሉተር መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መሐላ (ቃል ኪዳን) ማፍረስንም አስተምሯል።

ማሳሰቢያ፡- ካሁን በኋላ ማርቲን ሉተር ሳይሆን ሉተር እያልኩ እጽፋለሁ።

2.1 ሉተር በአዕምሮ የአለመረጋጋት ችግር የተዋጠ ግለሰብ ነበር

ጀርመንኛ ተናጋሪው የፈረንሳይኛና የጀርመንኛ ቋንቋዎች መምህር ፕሮፌሰር ፒተር ዋይነር ማርቲን ሉተርን ራሱንና ሌሎችን ስለ ሉተር የተጻፉ ዅሉተኛ ምንጮች በመጥቀስ martin Luther, Hitlers Spirituwal Ancestor. በሚል ርዕስ ለብዙ ዘመናት በጥቂት ሊቃውንት /Scholars ብቻ ይታወቅ የነበረውን የማርቲን ሉተር እውነተኛ ማንነት (ጸረ-ክርስትናና ጸረ-ክርስቶስ ተልዕኮ) የተራ ሰው ዅሉ እውቀት ይሆን ዘንድ ባበረከቱት መጽሐፋቸው ላይ ሉተር በልጅነቱ ዘመን በእናቱ እና በመምህራኖቹ እየተደበደበ ነበር ያደገው ይሉናል።

<u>ሉተር፡-</u> አንድ ቅንጣት ለውዝ ሰረቅህ ብላ እናቴ ደማ እስኪፈስ ገረፈችኝ [1] ማለቱንና በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ትምህርት ቤትም በቀን እስከ አሥራ አምስት ጊዜ ይገረፍ እንደነበር [2]

ፕሮፌሰር ዋይነር ጠቅሰዋል።

> ይህም አግባብ ያልኾነ ከባድ ቅጣት በዚህ ሕጻን ልጅ ባሕርይ ላይ ጥቁር ነጥቡን ጣለ። ድንጉጥ ወፍ ዘራሽና ተጠራጣሪም ሆኖ እንዲቀር አደረገው። የራሱን ጓደኞቹም የመንፈስ ጭንቀት እንደሚያሰቃየውና አዕምሮው ልክ እንዳልኾነ[3]

መስከረዋል።

> “ሉተር ጠቅላላ ነርቫዊ ቅንባሮው *(nervous system)* ውጥረት እንደነበረበት[4]

የሚያጠያይቅ አይደለም።

ሉተር ገና በልጅነቱ ምንኩሰናን የመረጠው ቤተሰቦቹን ጠይቆ ሲመለስ ድንገት በኃይለኛ አውሎ ንፋስ በመያዙና ከአጠገቡ የወደቀ መብትም በፈጠረበት ድንጋጤ የተነሳ ከወደቀበት ቦታ ሁኖ፡-

> “አውጭኝ አውጭኝ ቅድስት አኒ *(ከዚህ መዓት)* ካወጣሽኝ መነኩሴ እሆናለሁ[5]

ብሎ ሳያስበው በጭንቀት ሰዓት (July 2,1505 መሐላ በመግባቱ ነበር።

---

[1] Peter F. Wiener. Martin Luther. Hiders’s spitiual Ancestor. Gustay broukal press. 1985. ገጽ 19
[2] ዝኒ ከማሁ (Ibid) ገጽ 19
[3] ዝኒ ከማሁ ገጽ 19-20
[4] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20
[5] ዝኒ ከማሁ

> “ለዚህ ለፈራ ለተደናገጠ ስሜታዊና ያልተረገጋ ወጣት ከምንኩስና የከፋ ከባድ አሰልች ነገር ሊገጥመው አይችልም ነበር።”[6]

ብለዋል ፕሮፌሰር ዋይነር። ሉተር የምንኩስና ሕወትን “የመረጠበት” ምክንያት ገና በልጅነት ከደረሰበት ተደራራቢ አካላዊና አዕምሯዊ ሰቀቃ ለማምለጥ ከነበረው ፍላጎት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ከመራራ ሕይወት ገጠመኞቹ የተነሳ ስለዓለምና የሰው ልጅ ተፈጥሮ ክፉ አስተሳሰብ ስላላደረበት ዓለምን ንቆ የወሰደው ውሳኔ ሊሆን ይችላል።

ሉተር መነኩሴ ከኾነ በኋላ ከሌሎቹ መነኩሴዎች ጋር ሆኖ በመጸለይ ላይ እያለ መሬት ላይ ወድቆ “ሰይጣን አልያዘኝም ሰይጣን አልያዘኝም”[7] እያለ መጮህ ምናልባት በቤተሰብና በትምህርት ቤት ውስጥ ከደረሰበት ሰቀቃ አንጻር ይህን ክፉ የልጅነት ሕይወቱን በሰይጣን ከመጠቃት ጋር አይይዞት ስለዚህም ከእናቱና ከአስተማሪዎቹ የደረሰበት ቅጣት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምላሽ አድርጎ አስቦት ሊሆን ይችላል።

ብዙ ጌዜ በልጅነታቸው ጥላቻና ጥቃትን የተቀበሉ ሕጻናት በተለይ ሃይማኖተኛ ቤተሰብ ወይም ጎብረተሰብ ውስጥ ካደጉ ቅጣታቸው “ሰይጣን” ስለኾኑ ወይም ሰይጣን ስለያዛቸውና ስለዚህም የሚገባ እግዚአብሔራዊ ቅጣት እንደኾነ አድርገው ያስባሉ። “በምንኩስና ዘመኑ በነበረበት ገዳም ውስጥ የነበሩ ወጣት መነኩሳት ሉተርን በሰይጣን የተጠቃ አድርገው ያዩት ነበር።[8]

ሉተር ሕይወቱን በሙሉ በአዕምሮ አለመረጋጋት በሽታ ያሰቃየው እንደነበር ራሱ ከተላላካቸው ደብዳቤዎች ከጻፋቻው መጻሕፍትና በነዚህም ሥራዎቹ ስለ ነቢያት፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ክርስትና፣ ስለ ጦርትነት ፣ስለ ኢየሱስ፣ ስለ ጋብቻ፣ ስለ ግብረ-ሥጋ፣ ስለ መጠጥ፣ ስለ እምነት ወዘተ. ከተናገራቸውና የቅርብ ረዳቶቹ ስለዚህ ሰውዬ (ባሕርይ) ፀባይ ከተናገሩት ማወቅ ይችላል።

> Complete mental instability remained a key word to lis life. ፍጹም የኾነ የአዕምሮ አለመረጋጋት (ችግር) የሚለው ዕድሜ ልኩን አብሮት የኖረ ዓይነተኛ መገለጫ ነው። [9]
>
> ሉተር የነበረበት የአዕምሮ ጭንቀት ራሱን በሥራ በመጥመድ ወይም ከሚገባው በላይ ጊዜውን በጸሎት በማሳለፍ ኾኗልጊዜ ነገሮችን ከልክ በላይ በመሥራት ሊረሳ መሞከሩ የባሰውን የአዕምሮ ሕመሙን አባብሶታል።[10]

---

[6] ዝኒ ከማሁ
[7] ዝኒ ከማሁ
[8] ዝኒ ከማሁ
[9] ዝኒ ከማሁ
[10] ዝኒ ከማሁ

ሉተር በሠራው ኹሉ መጽሐፍ ቅዱስን መጻረር ብቻ ሳይሆን ይህን ተጻራሪ ሀሳቡንም በርሱ ውስጥ ያደረ እግዚአብሔር የሚናገረው እንደኾነ አድርጎ ሰብኳል። ዛሬ ሀገራችን ውስጥ የፈሉት ተቀጥረው የማያልቁ እርስ በርስ የሚጻረሩ የፕሮቴስታንት ውላጆች ክፍልፋይ አንጃዎች ለሚፈጽሙት ግፍ ኹሉ "ኢየሱስ ነገረኝ" ወዘተ. ጨዋታ ከዚህ የፕሮቴስታንት እምነት መሥራች ንግግሮች ጽሑፎች ቀጥታ የተቀዱ ወይም የዚህን ግለሰብ ንግግሮችና ጽሑፎች መሠረት ያደረጉ ናቸው።

ሉተር የአዕምሮ ጤንነቱ እጅግ የተዛነፈ ስለነበር ያስተላለፈው መልዕክትና ውጤቱም እንዲሁ የተዛነፈ ኾነ። ሉተር ዕድሜውን በሙሉ በተጻራሪና በኹሉም አቅጣጫ በሚስቡት ሕይወቱን በሚያጥለቀልቁት የሥጋ ፍላጎቶችና በእነዚህም በማይፈልጋቸው ስሜቶች መዋጡ ከእግዚአብሔር መራቁ በሚፈጥርበት ጸጸት የተዋጠ የውጊያ አውድማ ነበር። በ1521 ይህን የውስጥ መረበሽ በሚመለከት ሉተር እንዲህ ብሎ ነበር፦

> "በቃ ጸሎትን ችላ ከማለቴም በላይ አንዴ እንኳ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን አልናፈቅሁም። ከቁጥጥር ውጭ በኾነው ኹሉም ዓይነት ወሲባዊ አምሮት እየጋየሁ ነው። በመንፈስ ኃይል መሞላት ሲገባኝ በወሲባዊ አምሮት በጉምጀታ፣ በስንፍና፣ በሥራ ፈትነትና በእንቅልፋምነት ተውጫለሁ። "[11]

የሉተርን የአዕምሮ ሕመም የሉተር የሕይወት ታሪክ ፀሐፊው ፈንክ-ብሪንታኖ "የሚያደርጉትን የሚያሳጣ ቅዠት" ፕሮፌሰር በስኮህን ደግሞ ሉተርን "አዕምሮውን የሳተ"[12] ይሉታል።

2.2. ሉተር ሰይጣንን እንደማምለጫ ተጠቅሞበታል

የሉተር የአዕምሮ መበጥበጥ ራስን የመሳት ምልክቶች በዚህ የተገቱ አልነበሩም። ሉተር ከእሱ ጋር ያልተስማማ በእሱ ዐዲስ "ሃይማኖት" ያላመነን ሰው ወይም ማንኛውም ደስ ያላለውን ነገር ኹሉ ለመግለጽ የሚጠቀምበት ቃል "ከሰይጣን ነው" የሚል ነበር።

ዛሬ የማያውቁትን መልካሙን ቆንጆውን አግባቡን የአንድነት፣ የነጻነት፣ የኩራት (የእግዚአብሔራዊ ኩራት) ምንጭ የኾነውን ግን የማይስማሙበትን እነሱ ከፈቀዱት ውጭ ያለውን እግዚአብሔራዊነት ኹሉ "ሰይጣን" ነው የሚሉ የፕሮቴስታንቲዝም ፍልስፍና /ሃይማኖት/ አብዮት የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ጥቁር ፕሮቴስታንቶች ፕሮፓጋንዲስቶች ይህን የማያውቁትና የማይፈልጉትን ኹሉ "ሰይጣን" የማለት ጣጣን የተማሩት ከዚህ ሰውዬ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ሃሳብ ነው። ሉተር "በዲያቢሎስ ጭንቀት" (አእምሮ ሕመም) ይሰቃይ ስለነበር

---

[11] ዝኒ ከማሁገጽ 21 (as quated from Luther's Letters, nders edition volum 3 p.189)

[12] ዝኒ ከማሁ (as quated from Luther's Letters, nders edition volum 3 p.189)

> የደረሰበትን ያልተለመዱ የቅዠትና የመንቀጥቀጥ ችግሮች ኹሉ ቀጥታ ከሰይጣን ሥራ ጋር ያገናኛቸው ነበር። ስለዚህ ሰይጣን የሚለው ነገር ሕይወቱን የሚገዛው ዐብይ አሳቦት ኾነ”[13]

ፒተር ዋይነር እንዲህ ይላሉ፦-

It is one of the chief characteristics of Luther in his intellectual life, in his social intercourse, in speech, in writing and in preaching he always brought in the Devil–attributed far more influence and far more importance to’him than is warrwnted by scriptur, and by his writing gained for him in Germany a po

pularity which he have never before injoyed... all the slumbering germs of superstition both among the rude masses and the higher circles were by this means aeakened and set in motion.

> በአዕምሯዊ ሕይወቱ፣ በማኅበራዊ ግንኙነቱ፣ በንግግር በጽሑፍና በሰበካ ዘወትር ዲያብሎስን ማንሳት ከሉተር (ባህርይዎቹ) ፀባዮቹ ውስጥ አንዱና ዋናው ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ ከተፈቀደው ከሚገባው በላይ ኃይልና ዋጋ ሰጥቷል። በጽሑፉም ከዚህ ቀደም ጀርመን ውስጥ አይቶት የማያውቀውን ዝነኝነት ለራሱ ተጎናጸፈ... በዚህ ምንገድም ተዳፍነው የነበሩት የባዕድ አምልኮ ዘሮች ባልሰለጠነው ተራ ሕዝብም ኾነ በከፍተኛ መደቦች ውስጥ ተቀስቅሰው ሥራ ላይ ይውሉ ጀመር።[14]

ሉተር እጅግ ጥልቅ በኾነ ሰዎች ሳር ቅጠሉ ኹሉ ሊጎዱኝ ይፈልጋሉ በሚል ምክንያት የለሽ ስጋት (paranoia) የአዕምሮ በሽታ ይሰቃይ ነበር። ኹልጊዜ ሰዎች ሊጎዱት ሊቃወሙት ብቻ የሚፈልጉ አድርጎ ስለሚያስብ የእሱ ያልኾነ ሐሳብ የሚሰነዝሩትን ከእሱ ጋር የማይስማሙትን የሚጠላቸውን በትክክል የማይረዳውን እንዲሁም የማያውቀውንና የማይገባውን ኹሉ በቀላሉ ከሰይጣን ነው ማለት ይወድ ነበር። በሉተር ቤት፦-

> Every thing he disliked, cvery body who disagreed with him was inspired by Devil.
>
> እሱ የጠላቸው ነገሮች ኹሉ ከእሱ ጋር ያልተስማማ ኹሉ በሰይጣን የተመሩ ናቸው።[15]

---

[13] ዝኒ ከማሁ

[14] ዝኒ ከማሁ ገጽ 21-22

[15] ዝኒ ከማሁገጽ 21

ሉተር በሰይጣን መንፈስ የተመራ ሰው እንደነበር የበለጠ ግልጽ የሚያደርገው እንዲህ ማለቱ ነው።

> *Stan sleeps with me much more than my wife does*
>
> ከሚስቴ ይልቅ ሰይጣን አብዛኛውን ጊዜ አብሮኝ ይተኛል።[16]

2.3 ሉተር ጸያፍና ወሲባዊ የኾኑ ቃላትን ጠላቶቹን ለመቃወም በሰፊው ተጠቅሟል

ትልቅ "የእግዚአብሔር" ሰው ነኝ ከሚል የማይጠበቅ ጸያፍ ቃላትን እንደ አባት ገዳይ የሚጠላውን የካቶሊክ ሮማዊ ቤተ ክርስቲያን ለመስደብና ሕዝብንም በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ በጥላቻ ለማነሳሳትም በገፍ ተጠቅሟል። ሌላው ቀርቶ የሉተር የራሱን ሐሳብ ሕግ ወዘተ. ተጠቅመው የተቃወሙትን አድናቂ ተከታዮችን አልማረም። ሉተር በራሳቸው ጥንታዊ ብሉይ ኪዳናዊ አይሁዳዊ ሃይማኖት መጽናት የፈለገውንና ፕሮቴስታንቲዝምን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልኾኑ የጀርመን ቤተ እስራኤሎችን /አይሁዳውያንን/ ለማመን በሚያስቸግሩ አሰቃቂና ቆሻሻ ቃላት ዘልፏል። ሉተር ለእሱ አዲስ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም የማይመቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያትና ኢየሱስንም ሳይቀር ለመቃወም የተዋረዱ ቃላትን ያዘወትር ነበር።

በመቀበል ፍላጎት ላይ በተመሰረተው ጸረ-ካቶሊክ ፕሮፖጋንዳው በተከታዮች ዘንድ የበለጠ ክብደት ያገኘ እየመሰለው በጸያፍና ገዳይ ቃላቶች የታጀቡ ጽሑፎችንና ሰበካዎችን ይነዛ ነበር። አድናቂውና ተከታዩ የነበሩት ሚ ቡሊንገር ይህ የሉተር ጸያፍ ቋንቋ በተከታዮች ላይ ያሳደረውን ክፉ ተጽዕኖ እንዲህ ይገልጹታል።

> ከእሱ ጋር በሙሉ የማይስማሙትን ዅሉ ሰይጣን ይልቸዋል። ስሕተት ፈላጊ በመኾኑ እጅግ ሰፊ የኾነ ጥላቻና በጣም ትንሽ የጓደኝነት መንፈስ ስላለው... በጣም ብዙ ሰባኪያን ከሉተር መጻሕፍት ላይ የሰበሰቡትን ጸያፍ የስድብ መዝገበ ቃላት በየቤተ ክርስቲያኑ መቅደስ ቁመው ይነዙታል... ሰባኪዎችም እርኩስ ምሳሌነት የተነሳ በአሁን ጊዜ ጥሩ አቫንጀሊካል ሰባኪ መሆን የሚፈልጉ ዅሉ ስበካቸው በጸያፍ ስድብና ዘለፋ የታጨቀ መኾኑ አግባብ ይመስላቸዋል።" [17]

ሉተር ቤተ እስራኤላዊያንን በጓደኝነት መቅረብ የሚፈልግ ፕሮቴስታንት ጀርመናዊ መዘረፍ መዋረድ መጎዳት የሚፈልግ ብቻ ነው ብሏል። ቀጥሎም ጉዳቴ አነሰኝ የሚል ፕሮቴስታንት የሚከተለውን እንዲያደርግ ፕሮቴስታንታዊ ምክሩን ሰጥቷል። "ይህ በቂ

---

[16] ዝኒ ከማሁገጽ 22

[17] Janssen Johannes. History of the Germian People. From the close of the Middle Ages, volume 3 of 16 volumes. A.M.Christie, St Louis B Herder, 1910, v3 ገጽ 211.

ካልኾነ የቤተ እስራኤሎችን አፍ እንደ ሽንት ቤት እንዲጠቀምበት ይጠይቃቸው። ወይም ወደ ቤተ እስራኤሎች ፊንጢጣ ውስጥ ይግባና ያን ቅዱስ ነገር ያምልክ"። ዛሬ በፕሮቴስታንት ጸሎት ቤቱ የሚወርደውን ፀረ-ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የጥላቻ ሰበካ ልብ ይላል። የሉተርን ጸያፍና ተጋፊ በጥላቻ የተመረዘና ኃላፊነት የጎደለው ጽሑፉቹንና ሕዝባዊ ንግግሮቹን ያጠኑት ደራሲ ማርቲን ሉተር አሉ፦ "በጸያፍና ወሲብ ነክ በኾኑ ቃላት የተለከፈ ይመስላል"። በመቀጠልም እንዲህ ሲሉ ቃላቸውን ሰጥተዋል፦

> በል ሲለው በጣም ይናደዳል። ሲናደድም በጥሩ እንግሊዘኛ ሊገለጹ የማይችሉ ጸያፍ ቃላትን ያስታውክ ነበር።[18]

የሉተር እጅግ ጸያፍና ከመንፈሳዊነት ውጭ የኾኑ የቃላት አመራረጥ ዓለም Introduction to the literature of Europe በተባለ መጽሐፍ ላይ፦

> "የቃላቶች ግርድፍነት፣ ግድየለሽነት፣ ውበት የለሽነት፣ መረን መልቀቅና እርስ በዕርስ ተጻራሪነት የኃይማታዊ ሞራልን ከሥር መሠረቱ ያናጉ ከመሆናቸውም በላይ በጥንካሬና ሰው ሰርጾ በመግባት ስጦታቸው የተካካሱም አልነበሩም። እንዲያውም በእነዚህ ስጦታዎች ማነስ የተጻከሙ እንጂ።"[19]

ብለው ነበር። ሉተር በፀባዩ ያንጸባረቀው ከእውነተኛ የፍቅር እምነት የሚገኝ ሰላም ሳይሆን ቅጥ አንባሩ የጠፋው በጨለማ ውስጥ የሚመላለስ የተሸበረና ፍቅር የተነፈገው ፍጡር ባሕርይን ነበር።

> *There was noting godlike or holy him, there was little patience or human understanding; he loved to scream,shout, and blaspheme in the manner of the most vulgar German politician, such as out generation has seen more than enough.*
>
> እግዚአብሔራዊ ወይም ቅዱስ የኾነ ነገር ውስጡ የለም። ትዕግስተኛነቱ ወይም ሰብአዊ የመረዳት ችሎታው ዝቅተኛ ከመኾኑም በላይ በእኛ ትውልድ ውስጥ እስኪአንገፈግፈን ድረስ እንደታዘብናቸው በጣም ባለየ *(ባለጌ)* የጀርመን ፖለቲከኞች ኹሉ *መጮህ* መደንፋት የእግዚአብሔርን ስም በክፉ ማንሳት የሚወድ ሰው ነበር። "[20]

ሉተር ከመጽሐፍ ቅዱስና ከክርስቶስ ትምህርት ውጭ የኾነ፦

---

[18] Peter F, Wiener. ገጽ 22 (as quated from Maritain)
[19] Oconor Henty, Luther's Own Statements. NY: Benziiger Bros,. 3rd ed 1884 ገጽ 19 (see peter F. Wiener. ገጽ 23)
[20] Peter F, Wiener. ገጽ 22

> የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላ፣ ትዕግስት፣ ጀርነት፣ በጎነት፣እምነት፣የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው (ገላ ፭፥፳፪-፳፫) የሚለው ሊገባውና ሊቀበል የማይችል ሰው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ "ቁጡ ሰው ጠብን ያነሳሳል" ይላልና (ምሳሌ ፲፭፥፲፰)። ሉተር ግን የብዙ ዘመናትና የብዙ ትውልዶችን ውድመት ያመጣ ጸብ በሀገሩ ጀርመንና በምድረ አውሮፓ ላይ ዘርቶ አልፏል። ዛሬም ምዕራባውያን ራሳቸው ንቀው የተውትን ይህን ክፉ የመለያየት ርዕዮተ-ዓለም "ሃይማኖት" አንግበው ከዚያም የከፋ በራስ ጸጉር ልክ በዝተውና ተከፋፍለው በራስ ጸጉር ልክ የመከረኛ ሕዝባችን ልዩነቶች አባዙት። ሕዝባችንና አንድነቱን በልዩነት አጥሮች ከፍለው ለጸብ የሚያነሳሱ ብዙ ሺ ጥቁር ፕሮቴስታንታውያን ጅሀደኞች እንዲሁም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምስኪን ጀሌዎቻቸውና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ሀገራችን ውስጥ አሉ። ሉተር ለደም ፍላት ያለውን ፍቅር በቴብል ቶክ " Table Talk " የንግግር ስብስቦቹ ላይ እንደተዘገበው በኩራት እንዲህ ይለዋል:-

> *Rage acts as stimulant to my whole being. It sharpens my wits, puts a stop to the assult of the Devil and drives out fear. Never do I write or speak better than when I am in a rage. If I wish to compose, write pray and preach well, I have to be in a rage.*
>
> ደም ፍላት ጠቅላላ እኔነቴን እንደማነቃቂያ ሁኖ ያገለግለኛል። ችሎታዬን ይሰለዋል ሰይጣንም እንዳይጠናወተን ይረዳኛል በተጨማሪም ፍርሃትን ያባርርልኛል። ከሌላው ጊዜ ይልቅ በደም ፍላት ጊዜ የምጽፈውና የምናገረው በጣም ውጤታማ ነው።መግጠም መጻፍና መጸለይ ከፈለግሁኝ ደም ፍላት ውስጥ መሆን አለብኝ። [21]

በመሠረቱ በክርስትና እምነት ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሃይማኖት ውስጥ ደም ፍላትና ብስጩነት የተከለከለ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፦

> ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ሰው ሹሉ ለመስማማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ይሁን የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሰራምና (ያዕ ፩፥፲፱-፳)

ይለናል።

ደም ፍላት አዕምሮን የሚያጨገግና ሰው ከፊት ለፊቱ ያለውንና ያሰበውን ነገር ሹሉ በደንብ በግልጽ እንንዲያይ የሚያደርግ ስለዚህም (በኋላ) ቁጣ የፈጠረው የአዕምሮ ጭጋግ ሲለቅ ማለት ደም ፍላት ሲበርድ) የሚያስቆጭ የሚያሳዝን አፍራሽ ውሳኔን

[21] ዝኒ ከማሁ ገጽ 22 (as quated from Table Taik)

እንዲፈጽም የሚያደርግ የሰይጣን ጓደኛ ነው። በደም ፍላት ጊዜ የሚታሰቡና የሚፈጸሙ ነገሮች ኹሉ ውጤታቸው አስከፊ ነው።

የሉተር ሃይማኖት /አብዮት ፕሮቴስታንቲዝም በደም ፍላት ሰዓት ታስቦና ተጸንሶ የተወለደ በመኾኑ አስከፊ ውጤቱ ከ 400 ዓመታት በፊት ለምዕራብ አውሮፓ ከዚህም በኋላ የዚህ ክፉ እምነት ሰለባ በኾኑ በአውሮፓውያን ቀጥታ ቅኝ በተገዙ ነጭ ያልኾኑ ሀገሮች ውስጥ በተፈጠረው ማኅበራዊ ቀውስ እንዲሁም ዛሬ በእጅ አዙር በምዕራባውያን ቅኝ ሥር በወደቀችው ቅድስት ሀገራችን ውስጥ አየተንጸባረቀ ነው።

አሜሪካኖች እንደሚሉት፡- Anger is a state that starts with madness and ends with regret. ቁጣ በዕብደት ጀምሮ በአዕምሮ ጸጸት (ቁጭት) ያልቃል ማለት ነው። ሉተር በጸሎት ጊዜ እንኳን ሳይቀር በደም ፍላት ነው መጸለይ ያለበት። ግን ሉተር በስሕተቶቹ ብዙም የሚጸጸት ሰው አልነበረም። ሉተር ከውጭ ወደ ውስጥ ከመጠን በላይ የሚወስደው መጠጥ ብቻ አልነበረም የሚያረክሰው ከውስጥ ወደ ውጭ የሚወጣ እጅግ መራራና እጅግ ኢ-ክርስቲያናዊ የቃላት አመራረጡቹ ጭምር እንጅ።

ሉተር የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን "የዲያብሎስ ሸርሙጣ ቤተ ክርስቲያን"[22] ሲል አስከፊ በኾነ መልኩ ይገልጻታል። ልክ ገድል ወይስ ገደል ደራሲ ፋሽታዊና ሉተራዊ ስልት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የሽፍታዎችና የነፍሰ ገዳዮች ዋሻ እንዳሳት ኹሉ ሉተርም ከ 5 መቶ ዓመት በፊት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስን፡-

> *Liar, mad bloodhound, murderer, assasins of souls, arch knave dirty pig and devil's child, nay the devil himself*
>
> ዋሾ እብድ ውሻ ሕይወት አጥፊ ነፍስ ገዳይ የለየለት አጭበርባሪ ቆሻሻ አሳማና የዲያብሎስ ልጅ። ምን ይህ ብቻ ሰይጣን ራሱ ነው እንጅ። [23]

ማቴ.፭፥፶፪ እንዲህ ይላል፡-

> በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ኹሉ ፍርድ ይገባዋል። ... ደንቆሮ የሚለውም ኹሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።

ዛሬ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በጸያፍ አንደበታቸው የሙያረክሷትና የ 2 ሺ ዘመን ልምዷን እውቀቷን፣ ጥበቧን፣ ሥነ ጽሑፏ፣ ሳንንዊ መንፈስና ሀገራዊ ውለታዋን ክደው በድንቁርና በሚከሷት ያልተረጋ መንፈሳቸውን ከላይኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ አንጻር ሲመለከቱት መንፈሳዊ ጉልበት ያገኙ ይሆን?

---

[22] Grisar Hattmann luther translated. E.M Lamond Ed. Lugi Cappadelta, v. 4 of 6 volumes. London: Kegan Paul, Trench Trubener and co. 1917, ገጽ 288

[23] ዝኒ ከማሁገጽ 302

2.4 ሉተር አመክንዮ (reason) የሚጠላ ሰውም ነበር

የሉተር ሥራዎች ልክ የጡት ልጁ ሂትለር በሀያኛው ክፍለ ዘመን ጀርመንና አውሮፓ ውስጥ እንዳደረገው ዥሉ ልክ የጎሳ ርዕዮተ-ዓለሞችና የፕሮቴስታንት እምነቶች ሀገራችን ውስጥ እንደሚሠሩ ዥሉ የሚመሩት በተሳከረ ስሜታዊነት ብቻ ነው። ሉተር ለዚህ ስሜታዊነቱ ምክንያት ያለው የሰከነ ግንዛቤ አልነበረውም። አይወድም። ሉተር ስለመረጋጋት፣ ስለግንዛቤ፣ ስለ ምክንያታዊነት በተለይም ስለ አመክንዮ ያለውን ንቀት በራሱ አንደበት እንዲህ ይገልጸዋል።

> አመክንዮ የሰይጣን ታላቋ ሴተኛ አዳሪ ናት በተፈጥሮዋና በአኳኋኗ አስከፊ ሴት (ሴተኛ) አዳሪ ናት። ሽርሙጣ ናት.. በዲያብሎስ የተሾመች ሴት አዳሪ። አምን በቁስልና በቁምጥና የተወረሰች ከእግር ሥር ተጥላ መረገጥና መክሰም ያለባት ሴት አዳሪ... አስቀያሚ ትሆን ዘንድም ፊቷ ላይ ፋንድያ ለጥፍባት። በምትጠመቅበት ውኃ ውስጥ ሰምጣ መሞት አለባት። ... መከራ ይገባታል። በቤት ውስጥ በሚገኘው እጅግ ቆሻሻ ወደ ዥነው ቦታ ወደ ሽንት ቤት ልትገፋም ይገባል።[24]

ለሉተር "አመክንዮ ከእምነት ተጻራሪ ነው" የታወቁት ፈላስፋ ሚስተር ማርቲን የሉተርን ጸረ-አመክንዮ ፀረ- ምክንያት በባሕሪይ እንዲህ ያስቀምጡታል።

> ይህን ምዕራፍ የጠቀስኩበት ምክንያት ከጅምሩ ሐሰተኛ የኾነው ጸረ-ምሁራን የሃይማኖት አስተሳሰብ እንዴት የብዙዎችን ጭንቅላት በረቂቅና ቀጥታ ባልኾነ መንገድ በ19ኛው ክፍለ ዘመን (የነበረውን አስተሳሰብ) እንደመረዘው መለየቱ አስተማሪ ስለመሰለኝ ነው። ... ሉተር ሰውን አሰልቺና አስቸጋሪ ከኾነው የአዕምሮን የማሰብ ችሎታ ከመጠቀምና ሁሌም ተገቢ በኾነ መንገድ ነገሮችን ከማገናዘብ ኃላፊነት ገላገለው። "[25]

ጆንስ ዲቭሊዮ ቲ ግንዛቤ ወይም ውሳኔ ላይ ለመድረስ ጭንቅላትን የማሰብ ኃይልን መጠቀም ማለትም አመክንዮ ለሉተር፥-

> የማያዋጣና ቋሚነት የሌለው ነው። ዥሉ ነገር ከራሱ የግል የማይጨበጥ ሃሳብ ጋር ከተጋጨ አይቀበለውም። ... ሁላችንም የየራሳችን የግል እውነት ማወቂያ የእያንዳንዳችን የተናጥል የግል የውስጥ እምነት ነው ካልን አግባብና ግንዛቤያዊ ምርጫ ለመምረጥ አይቻልም። ይህም የክርስቲያንን አንድነት ይበትናል። [26]

በማለት ይህ ሃይማኖት ያደረሰውን ቀውስ The History of Western Philosophy, በሚለው መጽሐፍ በትክክል ገልጸውታል።

ክርስቶስ ባስተማረው ጊዜ ዥሉ ተከታዮችን እግዚአብሔርን በአዕምሮአቸው በልባቸው በነፍሳቸው ጥንካሬ እንዲወዱ ሉቃስ ፲፥፳፯ ላይ አስተማረ እንጂ እውር ድንብሱን በጭፍን ዝም ብላችሁ "በእምነት ብቻ" ተቀበሉኝ አላለም። እንዲያውም ኢየሱስ ማርቆስ ፲፪፥፳፰ ላይ

---

[24] Peter F, Wiener. ገጽ 23-24 (as quated from Erlangen v.16 p.142-148)
[25] Peter F, Wiener. ገጽ 25 (as quated from H. Maritain)
[26] Peter F, Wiener. ገጽ 25 (as quated from H. Halen)

“ከጳጳ አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደመለሳቸው አስተውሎ አኹሉ ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ማናኛይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው” ይላል። የሐዋ.ሥራ ፭፥፫ ላይ ኢየሱስ፦

በብዙ ማስረጃ ከመሞቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው

“በብዙ ማስረጃ እንጅ “በጭፍን እምነት” አይልም። በዮሐንስ ወንጌል ፳፥፳፬-፳፱ ከደቀ መዛሙርቱ ውስጥ አንዱ የነበረው ቶማስ የኢየሱስን ከእርነት በኋላ ተመልሶ መምጣትና ከአሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር መገናኘቱ ሲነገረው በጊዜው አልነበረምና አላመነም ነበር። ለማመንም ምክንያት ፈለገ። አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርትና ቶማስ በዚህ ጭቅጭቅ ውስጥ እያሉ፦

ኢየሱስ መጣ በመካከላቸው ቆሞ ሰላም ለእናንተ አላቸው። ከዚህም በኋላ ቶማስን ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ እጆችህንም አምጣና በጎኔ አግባው ያመንህ ሁን እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው (ዮሐ ፳፥፳፮-፳፯)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ፲፯፥፪ ላይ የክርስቶስ መከራ መቀበልና መሞት ሞትንም አቸንፎ ማረግ ለምን አስፈላጊ እንደነበር ከሦስት ሳምንት በላይ እንዳስተማረ ይገልጻል። ሐዋርያው ጳውሎስ ዝም ብላችሁ በኢየሱስ እመኑ አላለም ለምን ማመን እንደሚገባ አስረዳ እንጂ።

የሉተር በጭፍን እምነት ላይ የተመሠረቱ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትና በጭፍን እመኑ በእምነት ብቻ ተከተሉኝ የሚል እንቆቅልሽ አንድ ነገር ያስታውሰናል። በ 1995 (እ.ኤ.አ.) ክረምት ላይ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የመጀመሪያው ገጽ አንድ አባት ነው ከውኃ ጉድጓድ እየሳቡ የሚያወጡትን ውኃ የተሸከመ የባልዲ ገመድ በመበጠሱ ምክንያት ባልዲው ተመልሶ ጉድጓድ ውስጥ ለመግባት ሲሞክር በአየር እጦት እዚያው ጉድጓዳ ውስጥ ገብተው ይቀየራሉ።

በዚህ የተደናገጠ ሌላ ሰው እኒህን አባት ለመርዳት ሳያገናዝብ ወደ ጉድጓጉ ዘልቆ በመውረድ ይህም ሰው በአየር እጦት ምክንያት እዚያው ጉድጓድ ውስጥ ቀልጦ ይቀራል። በዚህ የተደናገጠች ሴት ልጅም ከኹለት ወገኖች ጸጥ ማለት አንዳችም ግንዛቤ ሳትወስድ አንዳችም ማስተዋል ሳታደርግ ከፍቅር ግን ከሞኝ ፍቅር በመጣ ቁርጠኝነት እርሷም ወደ ጉድጓ በመውረድ በኦክስጅን ማጣት በውኃ ተበልታ እንደቀረች ተዘግቧል።

ዛሬ “መውጫህን ሳታይ አትግባ” የአባቶቻችንን አነጋገር ያላስተዋሉ ኢትዮጵያውያን እህቶችና ወንድሞች “በእምነት ብቻ” የፈረንጅ መጤ መጠነ ብዙ ተጻራሪና ክፍልፋይ ስለዚህም አዋራጅ ግን ለጊዜው ደስ የሚያሰኑ የፕሮቴስታንት እምነቶች ውስጥ ዘለው የገቡ የተጠሙትን “የሕይወት ውኃ” ሳይጠጡ ይልቁንም የሕይወት ውኃን ፈልገው ከገቡበት አምራሪ ፕሮቴስታንታዊ ጉድጓድ ሳይወጡ በዚያው እየቀሩ ነው። ሌሎችም “በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን ሳታይ” የአባቶችን ምክር ሳያጤኑ እያዩ ግን ስለማያስተውሉ እየሰሙ ግን ስለማያደምጡ ስንቶች ከማይወጡበት የሞት ውኃ ጉድጓድ ፕሮቴስታንቲዝም ውስጥ ገብተው

እስከ ቤተ ሰቦቻቸው አለቁ። ሉተር በአግባቡና በወጉ በሰከነ አዕምሮ ማሰብ ባለመቻሉ በጊዜውም ያለጊዜውም እጅግ ጭልጥ ባለ ስሜታዊነት በመመላለሱ ስልጡን በኾነ መንገድ ማሰብ ማስተዋል ማገናዘብ (ሥልጡን መሆን) ባለመቻሉ ተጠየቃዊ /ሥነ-አመክንዮ /logical/ አስተሳሰብን ምክንያታዊነትን፣ ማገናዘብን ማስተዋልን እንዲጠላ አደረገው። ይህ ነበር እንግዲህ የፕሮቴስታንት ሃይማኖትና መሥራቹ ሉተር ማለት። ሉተር ከውጭ የመጣ መረጃን ዅሉ በተዛባና ከፋ ብቻ በሚያስብ አዕምሮው ስለሚተረጉመው በተፈጥሮ እውቀት ሊደረስበት የሚችለው ቀላልና አግባብ ነገር ዅሉ እጅግ አስከፊ ኃጢአት ወይንም የሰይጣን ዘይ እውቀት ምክንያት ሁኖ ይቀርባል።

ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነበው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳትና ለመፈጸም አልነበረም.. ጨርሶ። ይልቁንም ሊገነባው ይፈልግ የነበረውን ከክርስትና የተለየ “ጀርመናዊ አምላክ” እውን ይሆን ዘንድ የሚያስችሉትን ቁጥሮች፣ ምዕራፎች አንቀጾችና ምንባቦች ሲፈልግ ጨምሮ ሲፈልግ ቀንሶ ሲፈልግ ከዶ ሲፈልግ ዘሎ የእግዚአብሔርን ሳይሆን የራሱን የሰው ፍልስፍና እውን ለማድረግ ነበር አጥብቆ የታገለ።

በምዕራብ አውሮፓ በተለይም አሜሪካ ውስጥ ፕሮቴስታንቲዝም በአንጃ እየተከፋፈለ በመበታተኑና በዶክትሪን ሥር ሰደድ ልዩነቶች ሥነ-ልቡናዊ ጦርነቶችና ሹክቻዎች ብቻ አይደለም የሚታወቀው። ዛሬ ክርስቲያን ነን የሚሉ የክርስቶስን ስም የሚጠሩ አካል ሰዶማውያን የሚከፍቷቸው ጸሎት ቤቶች የሚታወቁት በፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያንነት ነው። ከዚህ እኩል የከፋ ሌላ ነገርም አለ። ይህም ፕሮቴስታንት ሃይማኖት እንደምናየው “Ku Klux Klan” ኩ ክሉክስ ክላን “ Christian Identity Movement” ክርስቲያን አይድንትቲ ሙቭመንት “World Church of The Creator” ወርልድ ኦፍ ዘ ክሬተር እና ሌሎችም እንደ አሸን አሜሪካም ውስጥ ኾነ ምዕራብ አውሮፓውስጥ በመፍላት ላይ ያሉ የሃይማኖት ሽፋን ያላቸው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በሚገርም ዅኔታ ዅሉም ማለት ይቻላል በፕሮቴስታንት ሃይማኖት ጥላ ሥር ራሳቸውን ማደራጀታቸው የዚህን ሃይማኖትና የዚህ ሃይማኖት ፈጣሪ ሉተር ዘረኛና ገዳይ ጦርነት አምላኪ እምነት ምን ያህል ርኩስ ዓላማ ላለቸው ድርጅቶች ተስማሚ እንደኾነ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሉተር በጎ በኾነ ነገር በቀላል ምርምር ሊደረስበት የሚቻለውንና የሚገባውን ነገር ለምሳሌ አመክንዮን መካዱና ሰው ዝም ብሎ በደመ ነፍስ ብቻ የመሰለውን እንደሚያምን ማንኛውንም ፀረ-አንድነትና ጸረ ክርስትና እምነት ዅሉ ቃላት በማሳመርና ለውስጣዊ ስሜት /emotion የሚቀርቡ ግን ደግሞ ለአመክንዮ /reason ጨርሶ እንግዳ የኾኑ ኃይማቶች እንደ አሸን እንዲፈሉ መንገዱን ከፍቷል።

በዘመናችን አፍራሽ ፕሮቴስታንታዊ ዲኖሚኔሽን ግብረ-ሰዶምና ክርስቲያናዊ ያልኾነ ልቅ ግብረ-ሥጋ መፈጸምን እንደቁርባን የሚቆጥሩ የሃይማኖቱን አባላት ሴቶች ዅሉ የፓስተሩና የረዳቶቹ ሚስቶች የሚያደርጉ የተወለዱ ሕጻናትንም እንደ እንሰሳ ወሲባዊ ጥቃት እየፈጸሙ በሃይማኖት ስም በኢየሱስ ስም ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ መከሰት የሉተር ፕሮቴስታንታዊ እምነት ከመጀመሪያውም ያልተባረከና ጥልቅ በኾኑ ፍልስፍናዊ ዶክትሪናዊ ችግሮች የታመሰ መኾኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የዘር ሐረጋቸው ከፕሮቴስታንቱ ሉተር የሚመዙ ጽንፈኛ/አምራሪ የሃይማኖቶችና አምባገነናዊ አገዛዝ አንድ ናቸው። ዶክትሪኑ ትክክል ባይሆንም ስሜት ባይሰጥም ለሕዝብ መከፋፈልና ለሀገር ጥገኝነትና ውድቀት መንስኤ ቢሆንም ሕዝብ ዝም በልና እመን ይባላል። ፕሮቴስታንትዝም/ ሉተሪዝም እውቀትንና ምክንያታዊነትን ይቃወማል።

2.5 ሉተር የወጣለት የሃይማኖት ትምክሕተኛ ነበር

ሉተር አስተሳሰቡ እምነቱ ኹሉ ነገሩ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከራሱ ጭንቅላት የመጣ መኾኑን ይክድ ነበር። የሚሠራቸው የሚናገራቸው የሚጽፏቸው ነገሮች ኹሉ ከእግዚአብሔር ስላለመሆናቸው የአዲሱ ሃይማኖት አፍራሽ ውጤቶች ብቻ አልነበረም መለኪያዎቹ ይልቁንም ጭንቅላቱ ሰርጾ የገባው እብሪተኛ ጭፍን ከተግባር የተፋታ እምነት እንጂ። ሉተር ይህን እጅግ ዓለማዊ በሥጋ ፍላጎትና በሥጋዊ ፍርድ ላይ የቆመ ትምህርት፥- “የማስተምረው ከሰማይ እንደመጣ እርግጠኛ ነኝ”[27] ብሎ ያርፋል። ሉተር አምባ ገነናዊ አስተሳሰብ ስለነበረውም፥-

> ማንም እኔ ካስተማርኩት ውጭ ካሁን በኋላ ቢያስተምር ወይም እኔን ባስተማርኩት ቢያወግዘኝ እግዚአብሔርን ነው ያወገዘው ስለዚህ የገሃነም ልክ መሆን አለበት።[28]

ብሎ ነበር። እንደተባለው፥-

> የሉተር የሐሰት ሃይማኖት ራሱን በተግባር ለመግለጽ ጊዜ አልፈጀበትም። ራሱ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ኹሉ በኾነ መለኮታዊ ኃይል እየተመራ የፈጸማቸው እንደኾኑ አስመስሎ ራሱን አሳመነ።[29]

የሚገርመው ተብሏል፥-

> ኹልጊዜ ሉተር “የእግዚአብሔር ቃል” የሚለው ከእግዚአብሔር ተገለጠልኝ ብሎ ራሱን የሚያኩራራበት የራሱ የግል የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎምና ዶክትሪን ነበር።[30]

ዛሬ በሀገራችን ውስጥ እንደ ወረርሽኝ በሽታ እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስ የተለቀቁት ክፍልፋይ ፈረንጅ ወለድ የፕሮቴስታንት እምነቶች ፕሮፖጋንዲስቶች፣ ጅሃደኞች፣ ካድሬዎች ለሚናገሩት ለሚጽፉት እጅግ በንቀት የበከተ እጅግ ጸረ-ጥቁር ሕዝብ እጅግ ፀረ-ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ስለዚህም ፀረ-ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳ አግባብነት ሽንጣቸውን ገትረው የሚገታሉ። እነዚህ የባዶ እምነት ባርያዎች በራሳቸው ትክክለኛ” ክፍልፋይ ፕሮቴስታዊ እምነት ያልተካተተን ኹሉ ገሃነም እንደሚወርድ የሚያስተምር ጨካኝ ሥርዓትን የብዙ ሀገር በቀል ኃይማኖች ምድር ኢትዮጵያ ላይ ለማራገፍና ፀጋዎቿን ለመግፈፍ በጅሀዳዊ ወኔ ያሸብራሉ።

ሕዝባችንም በፖለቲካ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም የተዳከመ መኾኑን ስላወቁና ምንም የመከላከያ እርምጃ እንደማይወስድ “እርግጠኞች” ስለኾኑ ያለምንም ፍርሃት ከአንደበቶቻቸው የሚወጣና በብዕሮቻቸው የሚንጸባረቁት መርዛም የጥላቻ ፕሮፖጋንደዳዎች

---

[27] O’conor Henery Luther and Lutherdom. Vol. 1, part 1 t, from 2nd rev. ed. Of german by Raymnd volz, somersel, England: Torch press, 1917, ገጽ 19 (scealso peter F, Wiener. P.25)

[28] ዝኒ ከማሁ ገጽ 20

[29] Peter F, Wiener ገጽ 25

[30] ዝኒ ከማሁ ገጽ 25

ኹሉ “ከኢየሱስ ነው” “እኔ አይደለሁም መጽሐፍ ቅዱስ ነው እንዲህ ያለው”... ይሉናል። ይህንም መጽሐፍ ለማስረገጥ በቁንጽል(out of context)ለመጠቃቀስ የተሳሳተ “እውቀታቸውን” ለማሳየት እጅግ እየተሰገበገቡ። አለቃቸው ሉተር ለሚናገረው/ለሚጽፈው ኃላፊነት የጎደለው መርዛማ ፕሮፓጋንዳ ማምለጫው የሚከተለው ነበር፦

> “ኢየሱስ የእኔ አለቃ ነው... እኔ አይደለሁም የእሱ ንጹሕ መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ። ”[31]

ሉተር ጭንቅላቱ ውስጥ የታጨቀው የውሸት እውቀት የእግዚአብሔርነትን ኃይል ያከናነበው መስሎ የሚሰማው ግለሰብ ነበር።

ትንቢተ ሚኪያስ ላይ ግን እንዲህ ይለናል፦

> ሰው ሆይ መልካሙን ነግሮሃል እግዚአብሔርም ከአንተ ዘንድ የሚሻ ምንድን ነው? ፍርድን ታደርግ ዘንድ ምሕረትንም ትወድድ ዘንድ ከአምላክህ ጋር በትሕትና ትሄድ ዘንድ አይደለምን? (ሚኪ.፮፥፰)

ኢየሱስ እኔ ከሌሎች እበልጣለሁ ብለን ከንቱ ውዳሴ እንዳንገባ (ማር.፱፥፴፫-፴፯) ያስጠነቅቀናል። ሉተር ግን በማይታክተው የሰይጣን አንደበቱ እንዲህ ይለናል፦

> “እኔ እስከማውቀው ድረስ በእናንተና በኹሉም መላዕክት ላይ ፈራጅ አኾነለሁ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለውም የእኔን ዶክትሪን የማይቀበል አይጸድቅም (የማስተምረው) የእግዚአብሔር እንጂ የእኔን ዶክትሪን አይደለምና። ”[32]

> “በአለፉት አንድ ሺ ዓመታት አግዚአብሔር ለእኔ የሰጠውን ስጦታ ከእኔ በቀር ለማንም ጳጳስ ሰጥቶ አያውቅም። ”[33]

የሉተር መልስ ሐሳዊ መሲሂዎች ስለመነሳታቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል፦

> ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን (የቅድስት ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናትን ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን ወዘተ.) እንኳን እስኪያስቱ ድረስ ታላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ (ማቴ.፳፬፥፳፬)።

ዛሬ ይህ ጥቅስ በአከራሪ ፕሮቴስታንታዊ የክሕደት ጦር ለተወገና ለወደቁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ብዙ በጣም ብዙ የሚያስተምረው አሉ። አስተውል!የተመረጡትን እንኳን እስኪያስቱ የሚለውን። ዛሬ አካባቶቻቸው ኃይማት ተፋልሰው በመጤ የሐሰት ፕሮቴስታንታዊ ማራኪ ግን አቅልጥ ፕሮፓጋንዳ ተታለው ሕመም ሳይኖር ፈውስን ለሰበኩ አስመሳዮች አድረው ስንቶች ታመሙ! ዋ! የቅድስት ኢትዮጵያ ተዋሕዶ እናት ቤተ ክርስቲያንን ክደው ለነጭ የባህል የበላይነት ፕሮቴስታንታዊነት የወደቁ ቀሳውስትና ዲያቆናት ማቴ.፳፬፥፳፬ን እንዲያስተውሉ ይሁን።

በመሠረቱ ግን “ድንቅ የመሥራት የመፈወስ” ኃይል ዛሬ መናፍቃን እንደሚነገሩን ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሥልጣን የሚፈጽሙት ሳይሆን በሥነ-ልቡና ትምህርት

---

[31] O’conor Henery ገጽ 20 (see peter F, Wiener. P 25)
[32] Janssen Johannes ገጽ 669-272
[33] Peter F, Wiener ገጽ 26

/psychology እና በሥነ-አዕምሮ /psychiatry ሙያዎች የሚታወቅና የሚሰራበትን ሳይንሳዊ ዘዴ በመጠቀም ማንም ስለ ጭንቅላት አሠራር /mind/ brain function/ እውቀት ያለው ሊያደርገው የሚችል ተራ ጥበብ ነው። የግድ አምራሪ ፕሮቴስታንት በመሆን የሚገኝ አይደለም።

ዛሬ ሕባችን ሊያጠፋበት ራሳቸውም ሊጠፉበት ብዙ መናፍቃን ወገኖቻችን የተጉለት ሃይማኖት "የእኔ ሃይማኖት /እምነት ካንተ ሃይማኖት እምነት ይበልጣል"። ኋላ ቀር ጭቅጭቅ በምዕራቡ ዓለም ውስጥ አስተዋሽ የመሌለውና መቶ የተቀበረ ድንቁርና ነው። ሃይማኖታዊ አፍራሽ ክርክር ዓለምን ከሳይንሳዊ ግንዛቤ አንጻር በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ዐይን ለማስተዋል በወሰነ አዲስ ምዕራባዊ ራዕይ መለወጡ ከተሰማ ቆየ። የሚያሳዝነው ይህ ምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ በአብዛኛው ከዘጠና ስድስት በመቶው ሕዝብ የእለት ተለት ኑሮ የሞተ ፕሮቴስታንታዊ ጽንፈኝነት ሀገራችን ውስጥ ሕይወት ዘርቶ አንሰራርቶ ዛሬ የሀገራችን ሕዝብ የልዩነት አጥር እየተከለ መቃብር እየቆፈረ ይገኛል። ሉተር

> "ከክርስቶስ ይልቅ በሚስቴና በተማሪዎቼ እምነት አለኝ"[34]

ብሏል። ዛሬ ያላወቁ አለቁ እንዲሉ የዚህን መሰሪ ሰይጣናዊ ሰው ማንነትን ያልተረዱ፣ ያላወቁ፣ ያልተነገራቸው፣ የተዋሹ፣ የተሸወዱና የተደበቁ አበሻዎች "እውነት" ነው ብለው ሐሰትን ይዘው የክርስቶስን ተቃዋሚ ሐሰተኛ ክርስቶስን ሉተርን (ማቴ.፳፬፥፳፬) እና ሐሰተኛ የተቃውሞ ሃይማኖት protestant religion (በእንግሊዘኛው protest ማለት መቃወም ማለት ነው። ፕሮቴስታንትዝም ማለት ደግሞ የተቃውሞ ሃይማኖት እንደማለት ነው) ይዘው ራሳቸውንም ሀገራቸውንም ያዋርዱበታል። በነገራችን ላይ "ተቃዋሚ" ማለት በግሪክኛ "ሰይጣን" ማለት ሲሆን በዕብራይስጥ ደግሞ ዲያብሎስ ማለት ነው።[35]

2.6 ሉተር ጸረ-ክርስቶስ ነው

ሉተር ከዚህም የከፋና የክርስትና እምነትን እውነተኛ ተከታዮችን ዅሉ የሚያዋርድ ሌላም ጸረ-ክርስቶስ ስለዚህም ጸረ-ክርስትና የኾኑ ዘለፋዎች አሉት፥-

> ክርስቶስን ሳይ ሰይጣን ያየሁ ይመስለኛል።
>
> ለክርስቶስ ትልቅ ጥላቻ አለኝ።
>
> ብዙ ጊዜ የክርስቶስን ስም ስሰማ እደነግጣለሁ።
>
> በመስቀል ላይ ሆኖ ሳስበውም ልክ በመብረቅ የተመታሁ ያህል ይሰማኛል፣ ስሙንም ከምሰማ የሰይጣን ስምን ብሰማ ይሻለኛል።[36]

ሉተር፥-

> እግዚአብሔር ቂል ነው
>
> "እግዚአብሔር እንደ እብድ ነው።[37]

---

[34] ዝኒ ከማሁ(as quated from "Table Taik" p 2397 b)
[35] ለይኩን ብርሃኑ ተነሥ Fetan printers Washington D.C. 1995
[36] Peter F, Wiener ገጽ 26 (see janssen 1172 also Maritan, Three Reference p. 169)
[37] ዝኒ ከማሁ ገጽ 27

የሉተር የተሰናከለ አዕምሮ በዲያብሎስ ኃይል የሚንቀሳቀስ ናላ ከቶ በንን ማሰብ ከቶ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር እንደተፈቀደው መተርጎም አይችልምና ፈሪሳዊያን በዘማዊነት የተያዘች ሴትን ወደ ኢየሱስ ወስደው ለተንኮላቸው ፍርድ እንዲሰጥ በጠየቁት ጊዜ “ከመሃከላችሁ ኃጢአት ያልሰራ የመጀመሪያውን ድንጋይ ይወርውር” በማለትበሰው ፈራጆችን አሳፍሮ የመለሰበትንና ኢየሱስ ከፈጸማቸው በፍቅር የተሞሉ ሥራዎች ውስጥ አንድ ትልቅ ሥፍራ የያዘውን በዮሐ.፲፩፣፫-፲ ላይ የተጻፈውን ይህን ክቡር ፍርድ ሉተር አቃሎና በሰይጣን አይዘህ ባይነት አጉብጦ ይተረጉመዋል። እንደ ሉተር ከኾነ ኢየሱስ ሴት አይቶ አምርም። ሉተር ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ የሚከተለውን የእብድ ፍርድ ሰጥቷል። “ክርስቶስ” አለ ሉተር፥-

> *Christ committed adultery first of all with a woman at the well about whom Saint John tells us. Was not every body about Him saying: What ever he has been doing with her? Secondly, with May Magdalcen, and thirdly with the woman taken in adultery whom he dismissed so lightly. Thus ever Christ, who was so righteous, must have been guilty of fornication he dide.*
>
> በመጀመሪያ ነገር ኢየሱስ ቅዱስ ዮሐንስ *(፬፣፯-፳ ላይ)* ከነገረን ሴት ጋር ምንጭ ዳር ዝሙት ፈጽሟል። አብሮት የነበረ ኹሉ “ከእሷ ጋር ምንም ያድርግ ምን” አላለምን? በኹለተኛ ደረጃም ከማርያም መቅደላዊት ጋር በሦስተኛ ደረጃም ዝሙት ፈጽማ ለፍርድ ፊቱ ከቀረበችለት *(ዮሐ.፲፩፣፫-፲)* እና በነጻ ካሰናበታት ሴት ጋር ዝሙት ፈጽሟል። ስለዚህ ጻድቁ ክርስቶስ እንኳን ሳይቀር ከመሞቱ በፊት ዝሙት የመፈጸም ጥፋት ሰርቶ መሆን አለበት። [38]

አስተውል! ዮሐንስ ወንጌል ፬፣፯-፳ ላይ፥-

> ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች ኢየሱስም ውኃ አጠጪኝ አላት ደቀመዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና... [39]

የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አጣሞ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከሰይጣን ባገኘው መላምት ሉተር እንደተረጎመው።

በሉተር ቤት ኢየሱስ እንደማንኛውም ሰው ተራ በተራ የሥጋ ፍላጎት የሚቃጠልና ሴት አይቶ የማይምር ነው። የደቀ መዛሙርት ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ መሄድ በሉተር ስንኩል አዕምሮ መሠረት ለተንኮል ኾነ ተብሎ ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ግብረ-ሥጋ ሊፈጽም ይችል ዘንድ “ምሳ እንግዛ በሚል ሰበብ ተከታዮቹ ኢየሱስና ሳምራዊቷ ሴት ብቻቸውን እንዲኾኑ ያመቻቹትና የተፈጸመ ነው። አስተውል ደግሞ ከመሞቱ በፊት እንጅ ከማረጉ በፊት አለማለቱን። ይህም ሉተር እንደ ዘመናችን ቁጥረ ብዙ ፕሮቴስታንታዊ አንጃዎች ኹሉ ኢየሱስን በአምላክነት ለመቀበል ችግር እንደነበረበት ያሳያል (ከጥቂት ዓመታት በፊት ከካናዳ

---

[38] ዝኒ ከማሁ (see “Table Taik” p. 1472, Weiner edition. P 107)
[39] ዝኒ ከማሁ (as quated from Erlangern v. 29, p. 96)

ፕሮቴስታንታዊ እምነቶች ውስጥ ትልቁ የሚባለው ቸርች መሪ ኢየሱስ አብዮተኞች እንጅ አምላክ አይደለም ብለው ነበር)። ሉተር ከክርስቶስ ይልቅ በሚስቴና በተማሪዎቼ የበለጠ እምነት አለኝ ማለቱን መዘንጋት የለብንም።

ዛሬ ሀገራችን ውስጥ እንደ መለስተኛ አምላክ የሚቆጠረውና ስለ እሱም የተጭበረበሩና አንድ ወገን ብቻ የኾኑ ወይም መልካም መልካሞቹን ንግግሮቹንና ጽሑፎቹን ብቻ የያዙ ወይም አምራሪ ፕሮቴስታንት ፈረንጆች ብቻ የጻፉትን መጠነ ሰፊ የትርጉም መጻሕፍት በከተማዎቻችን እንደ አሸን ከፈሉ ፕሮቴስታንታዊ መጻሕፍት ቤቶችና መደብሮች እየተዋሱና እየገዙ ወይም በስጦታ እያገኙ አዕምሮአቸውን በድንቁርና የሚያጣብቡ ወገኖቻችን ሉተር በ 1537 "በክርስቶስ አላመንኩም በማለት መጻፉን አያውቁም በመቀጠልም ሉተር እንዲህ ማለቱን አያውቁም፦

> እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እብድ የሚሠራውንን ይሠራል። እግዚአብሔር የሽማግሌዎችን አካል በማበደን የወጣቶችን አይን በመሰወር አለቅነቱን ያመቻቻል።
>
> እግዚአብሔርን ከአጭበርባሪ የተሻለ አድርጌ አላየውም።[40]

ሉተር ሕይወቱን ሙሉ በማይረካ የግብረ-ሥጋ ሱስ ተወጥሮ የኖረ ግለሰብ ስለመኾኑ ከራሱ ሥራዎች በዚህ ምዕራፍ ቀጥለን እናያለን። አሁን ግን መገንዘብ ያለብን ሉተር ኹል ጊዜ ለራሱ ሥጋዊ ተራ ስግብግብ ፍላጉቱ በሚያዋጣውና በሚስማማው መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን እንደተረጎመው ማወቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይለናል፦

> ስለዚህም ምክንያት በእውነት ያላመኑ ነገር ግን በዓመጽ ደስ ይላቸው የነበሩ ኹሉ ፍርድን እንዲቀበሉ ሐሰትን ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር የስህተትን አሠራር ይልክባቸዋል (2 ኛ.ተሰሎ፪፥፲፪)።

2.7 ሉተር ኃጢአት መሥራት ኩነኔ አይደለም ብሏል

ሉተር ለሰማይ ቤት ለገነት የሚያበቃው ሰውን የሚያድን መልካም ሥራ ጨርሶ አይደለም "እምነት ብቻ እንጂ። ለሉተር፦

> ሰው የሚሠራው ምንም አይደል የሚያምነው ነው ዋናው። [41]
>
> አምላክ ስለ ድርጊታችን ግድ የለውም የሚፈልገው እንድንጸልይና እንድናመሰግነው ነው። [42]
>
> ሉተር፦
>
> ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ኾነ እንዲሁ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው (ያዕ ፪፥፳፮)

የሚለውን አይቀበልም። ሉተር ከመጽሐፍ ቅዱስ ለራሱ የሚመቸውን ብቻ ነውና የሚቀበል። ሀገራችን ውስጥ ዛሬ "በይመቸኛል" መዝሙር የሚንበሸበሹት መናፍቃን ለራስ ደስ የሚል

---

[40] ዝኒ ከማሁ (see "Table Taik" No 963 Weiner edition. V1 p 487)
[41] ዝኒ ከማሁ ገጽ 28 (see Erlangen v. 29, p. 196)
[42] ዝኒ ከማሁ (see Erlangen v. 29, p. 196)

መሥራት (ለእግዚአብሔር ደስ የሚልለውን ሳይሆን) ከጡት አባታቸው ሉተር ነው በሲወርድ ሲዋረድ “ጥበብ” ያገኙት።

ሉተር ሰው በሥራው በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂ መኾኑን ካመነ ዝምትን ሰካራምነትን መተው ለሰው ፍልስፍና ፕሮቴስታንትዝም ሳይሆን ለእግዚአብሔር ተገዥነትን መቀበል ሊኖርበት ነው። ይህን ካደረገ ደግሞ ምኑን ተቃወመ? ምኑን ፕሮቴስት(protest) አደረገ? ምኑን ፕሮቴስታንት ኾነ?። አይችልም። ስዚህ፡-

> አዲስ ኃጢአት ብንሰራም ምንም አይደል እምነታችን ኃጢአትን ያስተሰርይልናል። [43]

ብሎ አረፈ አጅፊ።

ሰው በእምነቱ ደካማነት እንጂ በሥራው ደካማነት አይከሰንም የሚለው የሉተር ዶክትሪን፡-

> ተራው ሰው “መልካም ሥራ... ለነፍስ ጠቃሚ አይደለም ተብሎ ሲነገረው ደስ አለው። የዚህ አስተሳሰብ የማይቀር ውጤትም በጀርመን በፕሮቴስታንት ተሐድሶ ውስጥ ገና ከጅምሩ የሞራል የለሽነት ክስ አስከተለ። ይህንም የሞራል የለሽነት ክስ ለማስቀረትና ሕይወትን ትርጉም ያለው ለማድረግ ፍላጎት ነበር። ግን ሃይማኖት የልብ ነገር ብቻ አይደለም የሥራም ነው...። የፕሮቴስታንት የተሐድሶ እንቅስቃሴ በሥራ ኩነኔ የለም ድምዳሜ በኋላ የተከተለውን (የሞራለወ መጉደል) ማየት አልቻለም ነበር።[44]

ሉተር የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ከቆረቆረበት ጊዜ ጀምሮ የተከፈለበትን “ሰይጣን” ለኹሉ ነገር መጥራት ይወዳልና ደም ለማፍላት” ነበር።

“አንዳንዴ ኃጢአት መሥራት ጥሩ ነው ሰይጣንን የበሳጫልና ይህ በጹሑፎቹና ከአንደበቱ በወጡ የተረገሙ ቃላት ኹሉ የተናገራቸው የሚፈልገውን ነገር ከማስረዳት ይልቅ የአዕምሮውን መዛነፍ ቁልጭ አድርጎ ለታዛቢ የሚያሳይ የገሃነም ደጅ ሰውዬ እንዲህ ይለናል።

> ክርስትና ማለት ኃጢአት ብትሰራም ያልሰራህ ያህል መሰማቱ ነው ምክንያቱም የአንተን ኃጢአት በአንተ ፈንታ ክርስቶስ ይወስዳልና። [45]

ሉተር እምነትን ከኃጢአት ነጥሎ በመስበኩ አውሮፓ ውስጥ በኋላ ያመነ አስከፊ የሞራል መዳሸቅና ሥርዓት አልበኝነት ሰፍኖ ታይቷል። ኃጢአት በመሥራት ሰይጣናዊ ሱስ የተለከፈው ሉተር እሱ የሚወደውንና ከ 1517 ጀምሮ አብሮት የኖረውን ኃጢአት መሥራትና መደሰት ለምን ተከታዮቹም መውደድ እንዳለባቸው እንደሚከተለው አስረድቷል።

> “የክርስቶስ ምሳሌያዊ ሕይወቱ ሳይሆን ክርስቶስ ያሰበው ሀሳብ ነው ጠቃሚ” [46]

---

[43] ዝኒ ከማሁ ገጽ 29 (as quated from Erlangern v. 16, p. 254)
[44] Adolf von harnack Liberal Theology at its Height. Ed. Martun Rumscheidi, London Collins, 1989 ገጽ 222-223
[45] Peter F, Wiener ገጽ 29
[46] ዝኒ ከማሁ ገጽ 28

> “አዲስ ኃጢአት ብንፈጽም ምን አለበት? እምነት ኃጢአትን ኹሉ ይደመስሳል።” [47]

> “በዓለም ላይ ካለማመን (ፕሮቴስታንት ካለመሆን) በስተቀር ሌላ ኃጢአት የለም።” [48]

> *Some times it is neccssary to commit some sin out of batred and contempt for the Decil.*
>
> አንዳንዴ ለዲያቢሎስ ጥላቻና ንቀት ሲባል ኃጢአት መፈጸም ይገባል። [49]

> ኃጢአት መፈጸም ምን ክፋት አለው? [50]

> “ክርስቶስ የአንተን ኃጢአት እንደሚሸከምልህ ካመንክበት ጊዜ ጀምሮ እሱ በአንተ ፈንታ ኃጢአተኛ ይሆናል።” [51]

> ኃጢአተኛ ሁን። ኃጢአት ስትሰራም በድፍረት ይሁን ግን ስታምንም የበለጠ ደፋር ሁን።” [52]

> “ቅዱሳን ጥሩ የወጣላቸው ኃጢአተኞ መሆን አለባቸው። ደቀ መዛሙርቱ ራሳቸው ኃጢአተኞች ነበሩ። አዎ የለመዱ አጭበርባሪዎች... ነቢያትም ብዙ ጊዜ ከባድ የኾኑ ኃጢአቶችን እንደሰሩ አምናለሁ።” [53]

ዛሬ ሀገራችን ውስጥ እንደ አሸን የፈሉት ሉተራዊ ድርጅቶች ሕዝባችን ጸያፍ በኾነ ሥነ-ምግባራዊነት በጎደለው ኹኔታ በዳቦ በሐሰታዊ ፕሮፖጋንዳ በአዕምሮ መቆጣጠርያ ዘይዎች በማደንዘዝ በራሱ በቤተሰቡና በሀገሩ ላይ አሳመጹት። እግዚአብሔራዊ/መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባላኾኑ የሃይማኖት ማስካኛ ተግባሮች ላይ ተጠምደው ያለምንም ሐፍረትና የኅሊና ወቀሳ አቃፊ የሌለውንና እጅግ በሚዘገንኑ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ቀውሶች ውስጥ ተዘፍቆ በሚገኘው በገዛ ሕዝባቸው ላይ የሚፈጽሙት ኃጢአት ፕሮቴስታንታዊ/ሉተራዊ እምነታቸው ነጻ ያወጣናል ብለው አይደለምን?

2.8 ሉተር ራሱን መግዛት የማይችል ፍጡር ነበር

ሉተር ራስን መግዛት አንዱ የክርስቲያንነት መለያ መኾኑን ያውቃል። ግን ይህን ሕግ ከተከተለ የሚወደው መጠጥ ራሱን መሳትና “መዝናናት” አይችልም። ስለዚህም ሕይወት የሚገኝበት ሳይሆን እንደ ምኞቱ ደስ ያለውን (2ኛ ጢሞ. ፬፥፫) ሉተር መረጠ። ራስን መግዛት ትዕግስት ይላልና። ሙሉ ቀን ቁጭ ብ ስሰክር ዋልኩ ይለናል ሉተር።[54] ሐዋርያው ጳውሎስ ግን በማያሻማ ቋንቋ፦

---

[47] ዝኒ ከማሁ ገጽ 29
[48] ዝኒ ከማሁ
[49] ዝኒ ከማሁ (as quated from Erlangern v. 16.p.254)
[50] ዝኒ ከማሁ
[51] ዝኒ ከማሁ(Weiner editions, v. 25, p. 330)
[52] ዝኒ ከማሁ(as quated from Erlangern v. 62 .p.165
[53] ዝኒ ከማሁ
[54] Danifle Heinrich ገጽ 111

መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ (ኤፌሶን.፭፥፲፰)

ነበር ያለው።

ሉተር ራሱን መግዛት የማይችል ከእውነተኛ እምነት ጽናት በሚገኝ ድፍረት ሳይሆን ከእምነት ውጭ ከመሆን በሚገኝ ፍርሃትና የፍርሃትም ውጤት በኾኑት በራስ አለመተማመን ኹሉን ነገር መቃወም ማውገዝና ማሳደድ ማንነቱን የገለጸ ፕሮቴስታንት ነበር።

ሉተር አዕምሮውን በገዛው የመጠጥ ሱስ ተለክፎ ነበርና እንደ ሱሰኞች ኹሉ ከዚህ ገዳይ ሱስ ማምለጥ ሲያቅተው ገዥ በሥራ (አለመስከር)ሳይሆን በእምነት ኢየሱስን በመቀበል ብቻ የሚገኝ ይህም የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን በመቀበል ብቻ እንደሚሆን ተናገረ። ለሉተር፥-

> እግዚአብሔር መስከርን ከእለታዊ የኃጢአት ሂሳባችን ላይ እንደሚያሰፍረው አውቃለሁ ምክንያቱም መጠጥን ማቆም አይችልም። "[55]
>
> ብዙ የምጠጣው አዘውትረን ብዙ በመጠጣት የምዝናናው ለምን መሰላችሁ ሰይጣን ሊያሰቃየኝ ሊያላግጥብኝና በተዘጋጀ ጊዜ እኔ ቀድሜ ላላግጥበትና ላበሳጨው ስፈልግ ነው የምጠጣው"[56]

ይለናል ዳግም በተዛባ ናላው።

> ከበርግ (መንደር የመጣ) የቆየ ወይን ስለጠጣሁ ራሴን አሞኛል። የእኛ የዊትንበርግ ቢራም ቢራም ራስ ምታቴን እስካሁን ሊያሽለኝ አልቻለም። የሰራሁት ትንሽ ከመኾኑም በላይ በራስ ምታቴ የተነሳ ራሴ ማረፍ ስላለበት ያለ ምኞቴ ሥራ ፈትቼ ለመቀመጥ ተገድጃለሁ። "[57]

ያለው ጥሩ መረጃ ነው።

የሉተር ኹሉን ለእኔ ኹሉን የእኔ የጉምጀታ ልክፍት፥-

> አንድ ቆርቆሮ ቢራ ከጠጣሁ የቢራ ቤርሜሉን ራሱንም ያሰኘኛል። [58]
>
> እኔ ራሴን ለኅብረተሰብ ግፊት ለስካር ለወሲባዊ ፍላጎት አሳልፎ የመስጠት ችግር ያለብኝ ሰው ነኝ። [59]
>
> *What is needed to live in continence is not in me.*
>
> ራስን ተቆጣጥሮ ለመኖር አስፈላጊ የኾነ ነገር በውስጤ የለም። [60]
>
> የሌለ ድምጽ በመስማት ብቻ ሳይሆን በከባድ ራስ ምታት ስሰቃይ ከቆሁ ወር አለፈኝ። ምናልባትም የምጠጣው ወይን ወይም ምናልባት ዲያቢሎስ ያመጣው ህመም ሊሆን ይችላል። [61]

---

[55] ዝኒ ከማሁ

[56] Peter F. Wiener. ገጽ 33

[57] ዝኒ ከማሁ

[58] ዝኒ ከማሁ

[59] ዝኒ ከማሁ (see weinet edition, v.9 p. 215.13)

[60] ዝኒ ከማሁ

[61] ዝኒ ከማሁ

በማለት እንዲናዘዝ አድርጎታል።

ዛሬ ሉተር በ 1517 በመሠረተው የፕሮቴስታንቲዝም ኢንተርፕራይዝ ሃይማኖት ስም ግን ደግሞ በተለያዩ አንዳንዶም ተጻራሪ አንጃዎች ጥላ ሥር የተለያዩ ስሞች ለብሰው የሚንቀሳቀሱ የሀገራችን የሉተር የጡት ልጆች መናፍቃን ከሉተር የሚያስቱ ትምህርቶች ውስጥ ከሞላ ጎደል ዥሉንም እንዳሉ ተቀብለዋል። ከዘለሏቸው ነጥቦች አንዱ ያለ ልክ መጠጣትን ነው። እንዲያውም በሀገራችን ውስጥ የተነዙ አንዳንድ የፕሮቴስታንት አንቻዎች አስካሪ መጠጥን ጠቅላላ ይከለክላሉ።

2.9 ሉተር ከአንድ በላይ ማግባትን ፈቅዷል /ጋብቻ ክርስቲያናዊ መሆን የለበትም ብሏል

ሉተር ስለ ጋብቻ ቅዱስነትም ወራዳና ክርስቲያንዊ ያልኾነ አለመካከት ነበረው።

> ትዳር እንደማንኛውም ዓለማዊ መገበያየት ነው። ልክ እንደመብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መንቀሳቀስ፣ ፈረስ መጋለብ፣ ማውጋት ወይም ከአህዛብ ወይም ከአይሁዳዊ ጋር እንደመገበያየት ዥሉ የፈለግኋትንም ሴት ማግባት እችላለሁ። ይህን የሚከለክልን የቂሎች ሕግን አትቀበሉ። [62]

2 ኛ ቆሮ.፮፥፲፬ ላይ ግን ክርስቲያን ሰው ክርስቲያን ያልኾነን እንዳያገባ /እንዳታገባ የሚከለክል ምክር ተጽፎ እናገኛለን።

እንዲህ ይነበባል፦

> ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ ጽድቅ ከዓመጽ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው? ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር ምን መስማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?

ሉተር የግብረ-ሥጋ ጥም ግብረ-ሥጋ በመፈጸም ብቻ ሊረካ የሚችል ግን ደግሞ ሊቆጣጠሩት የማይቻል አደገኛ ኃይል ነው። ሉተር አንድ ወንድ ሚስቱ ወሲብን በከለከለችው ጊዜ ከቤት ሠራተኛው ጋር በመተኛት ራሱን ማርካት እንደሚችል ለተከታቹ ሰብኳል።

> ባልየው ለሚስቱ አብረሽ መተኛት ካልፈለግሽ ሌላ የሚፈልግ አለ ሚስትህ ካልፈለገች የቤት ሠራተኛህን ልትወሽማት ትችላለህ [63]

ብሏል ሉተር የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስራች።

ሉተር ይህ ጸያፍ እምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመኾኑን ስለሚያውቅ ስካር ሲሶ ልቡና አይነሳም እንዲሉ ከጥላቻ ከደም ፍላት ከስካር ከዝሙት ሕዝብን በሕዝብ ላይ ከማነሳሳት ወይም ደብዳቤዎችንና መጻሕፍትን ነጻ በኾነ ጊዜ አንዳንዴ አዕምሮውን ጸጸት ያነፍረው ነበርና እንዲህ አለ፦

---

[62] Martin Luther, Luther’s works, editions, Jarosalv Pelikan volumes 1-30 & Helmet T. Lehmann V. 31-55, St. Louis, Concordia publication House Volumes 1-30; Philadelphia; fortess, press volumes 31-55, 1955 p. 25 (see also Danifle Heinnich p 12, and Janssen Johannes v. 3 p 130)

[63] Danifle Heinrich ገጽ 17

> በመንፈስ መብሰል ሲገባኝ በሴሰኝነት ስሜት እየተቃጠልኩኝ ነው። ከቁጥጥር ውጭ በኾነው የሥጋ ፍላጎት እየነደድኩ ነው። እናም እዚህ በስንፍናና በመዝናናት ቁጭ ብዬ ጸሎቴን እረስቻለሁ። [64]

ሉተር ለሴቶች በአጠቃላይ አስፈሪና የሚረብሽ አመለካከት ነበረው።

በሉተር ናላ ሴት ልጅ ኼለት ጥቅም ብቻ ነው ያላት፦

> ሴት ልጅ አንድም ለትዳር አልያም ለሽርሙጥና መጠቀሚያ መሆን አለባት።[65]

> ሴቶች ከመፈጥፈጥ ብዛት ቢታመሙና ቢሞቱ ምንም አይጎዱም እስኪሞቱ ድረስ ይፈጥፈጡ የተፈጠሩት ለዚህ ነውና።[66]

ሉተር ራሱን "አስከፊ አፍቃሪ" እና ሦስት ሚስቶች ያሉት ግን ለመግባባት ፈቃደኛ ያልኾነ"[67] ይለዋል። ሉተር ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐሳቡን ቀይሮ ሲገባ ለፍቅር እንዳላገባ ተናግሯል። ያገባውም፦

> "ለሰይጣን ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ ነው"[68]

ሉተር ስለ ትዳር ስለ ሴቶችና ስለ ወሲባዊ ያለውን አስከፊ እንሰሳዊና በፀረ-ሴት ንቀት የተሞላ ሴትን እንደ ግብረ-ሥጋ መጠቀሚያ ዕቃ (Sex object) አድርጎ የማየት ፀባይ በሉተር ዘመን ብዙ ደናግል የካቶሊክ መነኩሴ ሴቶችን በፕሮቴስታንት አመጸኞች እንዲደፈሩ በር የከፈተ ሲሆን እንዲያውም የካቶሊክ መነኩሴ ሴቶችን በየገዳሙ እየዘሩ የደፈሩ ወንዶች "የተቀደሱና የተመረቁ ዘራፊዎች" እያለ ያሞጋግሳቸው ነበር።

የሉተር ጸረ-ሴት መልዕክትና ሴቶችን የወንድ የወሲብ ስሜትን ለማርካት የተፈጠሩ አድርጎ ማስተማሩ ዛሬም በአለንበት ዓለም ብዙ የፕሮቴስታንት እንጃ ኃይማት "ኢየሱስን እንወልደዋለን" ወይም "ወሲብ ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር መግለጫ ነው" ወይም "ኢየሱስ ከሁላችሁ ሴቶች ጋር እንድተኛ ነገረኝ" "ራዕይ አየሁ" ወዘተ. እያሉ "የቤተ ክርስቲያን" አባላት ሴቶችን የእነዚህ አንጃዎች መሥራቾች በጅምላ እንደሚወሽሙ የአደባባይ ምስጢር ነው።

የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ሃይማኖት አማኝና መሪ የነበረው ፈረንጅ ዴቭይድ ኮሬሽ ከጥቂት ዓመታት በፊት ዌክ በሚባል ትንሽ ከተማ ቴክሳስ አሜሪካ ውስጥ የእምነቱ ተከታይ የነበሩ ሴቶችን ኼሱ እያገባ ልጅ ይወልድባቸውና የወለዳቸውንም ልጆች ወሲባዊ ጥቃት ይፈጽምባቸው ስነበር ሕጻናትን በመጉዳት ጥርጣሬ (Child abuse) ለጥያቄ ተፈልጎ እጁን እንዲሰጥ ሲጠየቅ አሻፈረኝ በማለቱ ከአሜሪካ መንግሥት ወታደሮች ጋር በተደረገው የተኩስ ልውውጥ በተነሳው እሳት ከስሟል። አብረውት የነበሩ ከሰባ የበለጡ ፕሮቴስታንቶች /አማኞች (ብዙ ሕጻትና ሴቶችን ጨምሮ) ይህ ወንጀለኛ በመሸገበት በጸሎት ቤት ውስጥ በዚህ ጦርነት እንደ

---

[64] Peter F. Wiener ገጽ 21 (Luther's letters Enders edition v.1 pp. 66,67 and v.6 p.71)
[65] Danfile Heinrich ገጽ 124 (see also peter F. Wiener ገጽ 35-40
[66] ዝኒ ከማሁ ገጽ 304
[67] Peter F. Wiener ገጽ 39
[68] ዝኒ ከማሁ

ሞቱ ይታወቃል። ይህን በምዕራቡ ዓለም ጡት ባልጠቡ ሕጻናት ላይ ሳይቀር የሚፈጽም ለኢትዮጵያዊ ሕሊና ለመስማትም የሚዘገንን በሃይማኖት ስም የሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃትን ለመዘርዘር ራሱን የቻለ መጽሐፍ ያስፈልጋል።

በአዲስ አበባ በሚገኘው የሙሉ ወንጌል የጸሎት ቤት በ 1995 በመጨረሻ እሁድ ከሰዓት በኋላ በዕድሜ ጠና ያሉት ፓስተር ባሰሙት ሰበካ ልቅ የግብረ-ሥጋ ችግር የዓለም ብቻ ሳይሆን የሙሉ ወንጌል አማኞችም ችግር እንደኾነ አልሸሸጉም ነበር። ዛሬ አሜሪካ ምዕራብ አውሮፓና በሌሎች ክፍለ አህጉሮች ውስጥ ያሉት አንዳንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አንጃዎች ሉተር በፈቀደው (የግል ትርጉም) መሠረት ልቅ የግብረ-ሥጋ ባሕል፤ የእምነታቸው መገለጫ ነው። እንዲያውም አካለ ሰዶምን (ወንድ ለወንድ ወይም ሴት ለሴት) እንደሚፈቅዱና አንድ ወንድ ከሌላ ወንድ ጋር መገናኘት ብቻ ሳይሆን ከሴትም ጋር መገናኘት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስለኾነ ልንጠቀምበት ይገባል በሚል እንሰሳዊ ሩካቤ ሥጋን በራሱ እንደ አምልኮ መገለጫ መሥዋዕት የሚቆጥሩ አሉ።

በዓለም ላይ በሺህ የሚቆጠሩ የተለያዩ የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽኖች እንዳሉ ይታወቃል። ከእነዚህ አንጃዎች ውስጥ 1983 (እ.ኤ.አ) ወዲህ ሀገራችን ውስጥ ብዙ መቶዎች በመንግሥት እየተመዘገቡ ጉብተዋል። በፅፋ ተመዝግቦ ከመንቀሳቀስ ይልቅ በድብቅ መንቀሳቀስ የበለጠ ውጤታማ ያደርገናል በማለት በተለያዩ የእርዳታ የዲፕሎማሲ /ኢንቨስትመንት ... ሽፋን ሀገራችን ውስጥ የገቡትን ሳይጨምር ማለት ነው ሀገራችን ውስጥ የተተከሉት የፈረንጅ ፕሮቴስታንታዊ እምነቶች ሰለባዎች ከኾኑ ወገኖች ውስጥ ይህን "ሃይማኖት" የሚፈልጉበት ከብዙ ምክንያቶቻቸው ውስጥ አንዱ በተለይ ወንዶች ሴት ለማግኘት እንደኾነ ኹሉም የሚያውቀው የአደባባይ ምስጢር ነው።

ባለፉት አርባ ዓመታት ውስጥ በኢየሱስ "ሽማግሌነት ተገናኝተው ትዳር የመሠረቱት ጥንዶችን ብናይ ቢያንስ አንዳንዶቹ ትዳሮች የተመሠረቱት ወንዱ ቆንጆ በኾነች ኢትዮጵያዊነት አማኝ ወገን ላይ በወብቷ ያደረበትን ጉምጀታ ሥጋዊ ጥሬ ጥም በኢየሱስ በማላከክ "ኢየሱስ አንችን ለእኔ ፈቅዷል" ራዕይ አየሁ" የእኔ እንደሆንሽ ጌታ ነገረኝ" ወዘተ. በማለት ፈቃደኛ ያልኾነች እህትን በዚህ "ነገረኝ" "አሳየኝ" "መራኝ..." ጨዋታ ከፍተኛ ግፊት በማሳደርና ፍርሃትን በሴት ልብ ውስጥ በመልቀቅ በተገኘ "መፈቃቀድ" ነው ይባላል።

በወንዱ ላይ ምንም ዓይነት ስሜትና ፍላጎት የሌላትን ሴት ኹሉ "የእግዚአብሔርን ፈቃድ የጣሰች" "የጌታን ፈቃድ ሳይሆን የራሷን ፈቃድ ያየች ወዘተ. በማለት የአዕምሮ ጸጸት ሴቷ ጭንቅላት ውስጥ በመፍጠር ወይም የሴቷ ተቃውሞ ከሰይጣን በማስመሰል የዋህ ሴት ራሷን የሰይጣን መጫወቻ አድርጋ እንድታይና ይህን ትዳር ካልፈጸመች የኢየሱስ ልጅ እንደማትሆን በተለያዩ ተጽዕኖዎች በማስረገጥ እግዚአብሔር የፈለገውን ሳይሆን እነሱ የፈለጉትን የሚያገኙ አሉ። በዚህ የተነሳ የማትፈልገውና ደስተኛ የማትሆንበት ትዳር ውስጥ እንድትታሰር የኾነች ወገን ቤቷ ይቁጠራት። በዚህ ዓይነት "ጌታ ነግሮኛል ካላገባሁሽ..." ግፊት ምክንያት የአዕምሮ በሽተኞች የኾኑና እምነቱንም ለቀው የወጡ ብዙ እህቶቻችን አሉ።

በሴቶች ዘንድ ተፈላጊነት የሌላቸው ወንዶች ቆንጆ ከኾኑ ሴቶች ጋር በፕሮቴስታንታዊ "ትዳር" የሚተሳሰሩበት አንዱ ምክንያት ብልጣብልጥ ወንዶች የፕሮቴስታንት ጸሎት ቤትን ቆንጆ ሴቶችን እንደ መመልመያና ማጫ ስለሚጠቀሙበት ነው። ዛሬ በየፕሮቴስታንቱ ጸሎት ቤት

በፖስተሮችና በአማኞች ፊት ቀርበው "እንዲባርኩ ለቁጥር የሚታክቱ "እጮኛሞች" ወደ መድረክ ወጥተው ከሕዝቡ በመተዋወቅ በጭብጨባ ይበል ይበል ይባላሉ። አስተውላለሁ አዲስ አበባ ውስጥ ከፕሮቴስታንት ጸሎት ቤቶች አንዱ ከኾነው አንጃ ጸሎት ቤት ውስጥ ፓስተሩ "ዓላማችን ማጋባት ነው" ብለው በፈገግታ እንደተናገሩ። በተለይ ወንድ "ምዕመናን" የኮለኮሏቸውን (የኮረኮሯቸውን) ያህል አስቋል የደስታ ሳቅ የፕሮቴስታንት መሥራች ሉተር በራሱ እንደበት፥-

> የሥጋ ወሲባዊ ፍላጎታችን ልጃገረዶችና ሴቶች እስካሉ ድረስ ማርካት አለብን[69]

ብሎ ተናግሯል።

ሉተር እሱ በፈጠረው አስከፊ ሃይማኖት ምክንያት የደረሰውን የሞራል ውድቀት አምኗል።

> እንደዚህ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያስከትል መኾኑን ቀድመን ብናውቅ ግብዝነት ቅሌት ይሉኝታ ቢስነት ቅዱስ ቦታዎችን ማርከስና ከፋት እንደዚህ የሚከተል መኾኑን ብናውቅ ኑሮ ማን ይሰብክ ነበር። አሁን ግን የጥፋታችን ውጤት እያየን ነው።[70]

ሉተር በመቀጠል እንዲህ ብሎ ነበር፥-

> ኹሉም ሰው አዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ብጥብጥ አስነሳ እያለ ያማርራል... ከተነሳ ዘንድ ኹሉ ከድሮው የከፋ ሆኗል።[71]

ይህ አባባል የሚገርም ኹኔታ አውሮፓ ውስጥ ከኾነ ከ 500 ዓመታት በኋላ በሀገራችን ውስጥም እውነት ሁኗል። እራስመስ የተባሉ ፕሮቴስታንት በደረሰባቸው ከፍተኛ የሞራል ውድቀት በጊዜው እንዲህ ብለው ነበር፥-

> ኹሉ ነገር በከፋ ኹኔታ እየቀ፥ጣለ ነው መተከል ያለበትን ይነቅላሉ። ቤቱን ለማጽዳት ያቃጥላሉ። ሞራል ቀርቷል በምኞት መበስበስና ዝሙት ከመቼውም ይልቅ ቀጥሏል ሥርዓት ሕግ ዲሲፕሊን የለም። "[72]

ሉተር ስለ ትዳርና ስለ ወሲብ የሚከተለውን ብሏል፥-

> ትዳር እንደማንኛውም ነገር ውጫዊ አካላዊ ነገር ነው። [73]
>
> ትዳር እንደማንኛውም ዓለማዊ ተግባር ውጫዊ ጉዳይ ነው። [74]
>
> ሥጋዊ ፍላጎታችን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ስለዚህ አንድ ሰው ጎረቤቱ ላይ ኃጢአት ይሠራል እንጂ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሊሠራ አይችልም። [75]
>
> ወንድ ልጅ ከአንድ በላይ ሚስት እንዳይኖረው አልተከለከለም።[76]

---

[69] Grisar Hartmani V. 4 p. 145
[70] Danifle Heinrich ገጽ 26
[71] ዝኒ ከማሁ ገጽ 25
[72] ዝኒ ከማሁ ገጽ 9
[73] Peter F. Wiener ገጽ 37
[74] ዝኒ ከማሁ
[75] ዝኒ ከማሁ
[76] De Wettr v,2, p 459 (see also petter F. Wiener p.38)

> እኔም መነኩሴ ተጋብቻለሁ። እንዳገባ ያስገደደኝ ልዩ ምክንያት ባይኖረኝ ኑሮ አላገባም ነበር። ያገባሁት ግን ከሞኝነታቸው የተነሳ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዳያገቡ የከለከሉትን የዲያብሎስ ማደሪያ ተቃዋሚዎቻችን ልዑሎችን ጳጳሳትን ደስ እንዳይላቸው ነው። እግዚአብሔርን የሚያስደስትን ግን የነሱን ደም የሚያፈላ በደንብ የታሰበበት ዘዴ ባገኝ በሙሉ ልቤ የከፋ ቅሌት እፈጥር ነበር። "[77]

2.10 ሉተር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሃላ ማፍረስን አስተምሯል

ሉተር ራሱ የካቶሊክ መነኩሴ ስለነበርና በገባውም ክርስቲያናዊ መሐላ መሠረት ከሴት መድረስ ስለማይችል "አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ" እንዲሉ መሐላን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው በመናገር ራሱ ሊፈጽመው የፈለገውን ኃጢአትና ሊያፈርሰው የፈለገውን የምንኩስና ቃል ኪዳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደኾነ በሐሰት መመስከር ነበረበት ስለዚህ፦

> የማንም መነኩሴ መሐላ ለእግዚአብሔር ጠቃሚ አይደለም። ቄሶችና መነኩሴዎች መሃላቸውን እንዲያፈርሱ ግዳጅ አለባቸው። በተለይ ይህ የእግዚአብሔር ፍጥረት እንዲበዛ የሚያደርግ ከኾነ። [78]

ብሎ አረፈ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በማቴ. ፭፥፴፫ ላይ መሐላችንን ለጌታ እንድትሰጥ ሐዋርያ ጳውሎስ ይማጸናል። መጽሐፈ መክብብ ፭፥፬-፮ ይላል፦

> ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ ትፈጽም ዘንድ አትዘገይ የተሳልኸውን ፈጽመው

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለቱ ሲደርስለት በስለቱ መሠረት ጸጉሩን ቆርጧል (ሐዋ. ሥራ. ፲፰፥፲፰)። መሃላ ማፍረስ እግዚአብሔርን እንደሚያስከፋ እርግማን እንደሚያስከትል ሚልክያ ፩፥፲፬ ላይ ተጽፏል። መሐላን ማጠፍ ሞትን እንደሚያስከትል ሕዝቅኤል ፲፯፥፲፯ ላይ እንማራለን።

የሉተር አስከፊ ማንነት የሚጎላ ሰው ያለ ግብረ-ሥጋ መኖር ከቶ እንደማይቻል ለማስረገጥ ለተከታዮቹ እንዲህ ያለው ነው፦

> ሚስት እስኪያገቡ ድረስ መቆጣጠር የማይቻለውን የተፈጥሮ ወሲባዊ ፍላጎት ማርካት ይቻላል። [79]

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን 1 ኛቆሮ.፯፥፯-፱ ላይ እንዲህ ይለናል፦

> ሰው ኾኑ፤ እንደ እኔ ያለትዳር ቢኖር ደስ ይለኛል። ... ላላገቡት እንደ እኔ መሆን ጥሩ ነው እላቸዋለሁ። ካልቻሉ ግን ያግቡ

በመሠረቱ እንኳን ሃይማኖት ይቅርና ማንኛውም የሰው ልጅ በየዕለቱ በተናጠልም ኾነ ከሌሎቸች ጋር የሚወጥናቸው ተግባራት ትርጉም ይኖራቸው ዘንድ ከፍጻሜ ይደርሱ ዘንድ በቃል ኪዳን/በሕግ መግዛት እጅግ አስፈላጊ ነው። ሰዎች ዋሻ ውስጥ ሳር ቅጠሉን እያመለኩ

---

[77] Peter F. Wiener ገጽ 39-40
[78] Danifle Heinrich ገጽ 9
[79] Peter F. Wiener ገጽ (as quated from Erlangen v.33p. 327)

በጎሳዎችና መሰል ጦርነቶች የገደሏቸውን የጠላት ሚስቶች እየወረሱ ማንነታቸውን በሚገለጹበት ዘመን ሕግ የለሽነትን ራሱ ሕግ ነበር።

በምንኖርበት ዘመናዊ ዓለም ግን የሉተር ሕግ የለሽ የንመጁለትን ችሉ የመፈጸም ፈቃድ ጎብረተሰብን ወደ ጨለማ ዘመን ይመልሰዋል። ይህ ዓይነቱ ዛሬም በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚገኙ የተለያዩ የፕሮቴስታንት ድርጅቶች የሚገፋው ፀረ-ክርስቲያናዊ የልዩነት ትምህርት ሥርዓት አልበኝነትን የአብዛኛዎቹ የፕሮቴስታንታዊ ክፍልፋዮች/ዲኖሚኔሽኖች ዓይነተኛ መገለጫ እያደረገ ነው። ፕሮቴስታንታዊ ሕግ የለሽነት /የእንሰሳት ሕግ የህገራችን ከተማዎችንም አሜሪካውያን እንደሚሉት "የከተማ ጫካ/urban jungle/ እያደረጓቸው ነው። ድርጅታዊና ጉልበት እስካላቸው የአዕምሮ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችንና ፕሮፖጋንዳን ሳያሰልሱ እስከተጠቀሙና መንፈሳዊ ኪሳራ የህገራችን መገለጫ ሁኖ እስከቀጠለ ድረስ የአበሻ ነፍስ በማደን በመግደልና እንደገና የተወለደ በማድረጉ ግፋቸው ይቀጥላሉ።

ሙሉ መጽሐፉን ለማግኘት @tsionfish

BookX. ብለው ይዘዙ።